
Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHIINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አካባቢ ሳይንስ

## ሁለተኛ ክፍል

## የተማሪ መጽሐፍ



Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource

# አካባቢ ሳይንስ
# ፪ኛ ክፍል
# የተማሪ መጽሐፍ


**አዘጋጅ**

ሞገስ ሸንቁጤ

ቀማቸው ጥላሁን

መልካሙ ተስፋዬ

አቤኔም ይርዳው

**አርታኢና ገምጋሚዎች**

ሰሎሞን ወንድሙ

በላይ በለጠ

ሙሉነህ ተክለብርሃን

ጌታሁን ጌታቸው

አሊ ከማል

**አስተባባሪ**

ጌታቸው ታለማ

**ሥዕላዊ መግለጫ እና ገጽ ቅንብር**

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ (ሲሳይ ደጉ)



2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource

© 2015 ዓ.ም  የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት የተጠቀመባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን፡፡

# ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽኃፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽኃፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource

# ማውጫ ገጽ


ምዕራፍ አንድ ........ 1

የወረዳችን መገኛ ........ 1

1.1. የመገኛ ምንነት ........ 2

1.2. የአንጻራዊ መገኛ ምንነት ........ 4

1.3. የወረዳችን አንጻራዊ መገኛ ........ 8

1.4. በወረዳችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ ........ 12

1.5. የወረዳችን አዋሳኝ ወረዳዎች መገኛና ስማቸው ........ 14

ምዕራፍ ሁለት ........ 19

ሳይንስን መገንዘብ........ 19

2.1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችና የስሜት አካላት ........ 20

2.2. የቁሶች አካላዊ ባህርያት ........ 27

2.3. የብርሃን ምንጮችና ባህርያት ........ 35

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource

ምዕራፍ ሦስት ........................................................ 45
ተፈጥሮአዊ አካባቢ ................................................... 45
3.1. የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ..........................................46
3.2. በወረዳችን የሚገኙ ዕጽዋት ..............................................57
3.3. በወረዳችን የሚገኙ እንስሳት ............................................68
3.4. በወረዳችን የሚገኙ ቁሳዊ ሀብቶች......................................77
3.5. የወረዳችንን አካባቢ መንከባከብ ........................................81

ምዕራፍ አራት ........................................................ 90
ማኀበራዊ አካባቢ ..................................................... 90
4.1. የቤተሰብ አባላትና ፍላጎታቸው ........................................91
4.2. በትምህርት ቤት ተግባራትን በጋራ
ማከናወንና የአቻ ግንኙነትን ማዳበር........................................111
4.3. ንጽሕናና የግል ጤና...........................................................118

ምዕራፍ አምስት...................................................... 131
ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች.......................................... 131
5.1. የመንገድ ደኅንነት...........................................................132
5.2. ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ .......................................................141

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# ምዕራፍ አንድ
# የወረዳችን መገኛ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የመገኛ ምንነትን ትገልጻላችሁ፡፡
- የአንጻራዊ መገኛን ምንነትን ትገልጻላችሁ፡፡
- የምትኖሩበትን ወረዳ አንጻራዊ መገኛ ታመለከታላችሁ፡፡
- የምትኖሩበትን ወረዳ መገኛ ከአጎራባች ወረዳዎች አንጻር በንድፍ ካርታ ላይ ታሳያላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን መገኛ በንድፍ ካርታ ታመለክታላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚገኙትን መንደሮችን በማመልከት ስማቸውን ትገልጻላችሁ፡፡
- የወረዳችሁን አዋሳኝ ወረዳዎች ትዘረዝራላችሁ፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

1.1. የመገኛ ምንነት

1.2. የአንጻራዊ መገኛ ምንነት

1.3. የወረዳችን አንጻራዊ መገኛ

1.4. በወረዳችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ

1.5. የወረዳችን አዋሳኝ ወረዳዎች መገኛና ስማቸው

# 1.1 የመገኛ ምንነት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የመገኛ ምንነትን ትገልጻላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- መገኛ
- አቅጣጫ

መገኛ ምንድን ነው? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ

መገኛ አንድ ነገር የሚገኝበት ትክክለኛ ስፍራ ወይም ቦታ ነው፡፡ የአንድን ስፍራ መገኛ አቅጣጫዎችን በመጠቀም መግለፅ እንችላለን ፡፡

## አቅጣጫ ምንድን ነው?

አቅጣጫ ማለት አንድን ቦታ ለመጠቆም ወይም ለማመልከት የምንጠቀምበት መንገድ ነው።

የአንድን ቦታ ወይም ነገር መገኛ ለመግለፅ የሚከተሉትን አቅጣጫ አመላካች ስያሜዎችን መጠቀም ይቻላል።

- ፊት ለፊት
- ጀርባ
- አጠገብ
- ግራና ቀኝ
- ጎን
- ፊትና ኋላ

### የቡድን ውይይት 1.1

በቡድን በመሆን በሚከተሉት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የቡድናችሁን ሐሳብ ለመምህራችሁ አቅርቡ

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የክፍላችሁ ጥቁር ሠሌዳ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?
2. የክፍላችሁ መስኮት በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?
3. ቤተ-መጻሕፍቱ ከመማሪያ ክፍላችሁ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?
4. ሰንደቅ ዓላማው ከቢሮው በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



**መልመጃ 1.1**

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. መገኛን በአቅጣጫዎች ማወቅ ይቻላል::
2. አንድ ነገር ያለበት ቦታ መገኛ ይባላል::
3. ግራና ቀኝ አቅጣጫን አያመለክትም::

## 1.2. የአንጻራዊ መገኛ ምንነት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የአንጻራዊ መገኛ ምንነትን ትገልፃላችሁ::
- አንጻራዊ መገኛን በምሳሌ ታብራራላችሁ::

**ቁልፍ ቃላት**

- አንጻራዊ መገኛ
- መሠረታዊ አቅጣጫ


### አንጻራዊ መገኛ ምንድን ነው?

አንጻራዊ መገኛ አንድ ቦታ ወይም ነገር በአካባቢው ካሉት ቋሚ ነገሮች ለምሳሌ ተራራዎች፣ ወንዞች፣ መንገዶች፣ ሕንፃዎች እና ሌሎች ነገሮች አንጻር የሚገኝበትን ስፍራ አመላካች ነው::

አንጻራዊ መገኛ የምንኖርበትን አካባቢ መገኛ ከሌሎች ቦታዎች አንጻር ለማሳየት ይጠቅማል፡፡

ተማሪዎች ከዚህ በታች የሚገኙትን ስዕሎች በትኩረት ከተመለከታችሁ በኋላ ከታች ላሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን ደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡

ሀ. በስዕሉ የሚታዩት ሰዎች ከመኪናው በየትኛው አቅጣጫ ቆመዋል?




ሥዕል 1.1 አንፃራዊ አቅጣጫን መግለጽ

ለ. በስዕሉ የሚታዩት ተማሪዎች ከሕንፃው በየትኛው አቅጣጫ ይታያሉ?



ሥዕል 1.2 አንፃራዊ አቅጣጫን መግለጽ

ሐ.ውሻው ከድመቷ በየት በኩል ይገኛል?



ሥዕል 1.3 አንፃራዊ አቅጣጫን መግለጽ

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



መ. ከልጆቹ በስተቀኝ በኩል ምን ይገኛል? በስተግራስ?



ሥዕል 1.4 አንፃራዊ አቅጣጫን መግለጽ

## መልመጃ 1.2

ሀ. የሚከተለውን ስዕል በመመልከት ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡




ምስል 1.4 አንፃራዊ አቅጣጫን መግለጽ

1. ሀውልቱ ከሀንፃው በየት በኩል ይገኛል?

2. ሰማያዊው መኪና ከነጩ መኪና በየት በኩል ይገኛል?

3. ህንፃው ከሀውልቱ በየት በኩል ይገኛል?

4. ነጩ መኪና ከሰማያዊው መኪና በየት በኩል የት ይገኛል?

## 1.3 የወረዳችን አንጻራዊ መገኛ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የምትኖሩበትን ወረዳ አንጻራዊ መገኛ ታመለክታላችሁ፡፡
- የምትኖሩበትን ወረዳ መገኛ ከአጎራባች ወረዳዎች አንጻር በንድፍ ካርታ ላይ ታሳያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ወረዳ
- ንድፍ ካርታ

ተማሪዎች! ባለፈው ንዑስ ርዕስ ስለአንጻራዊ መገኛ ምንነት ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ እንዴት እንደምትገልጹ ትማራላችሁ፡፡


ወረዳ ከክፍለ ከተማ በታች የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

## የቡድን ውይይት 1.2

ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሃሳብ ለመምህራችሁ በቃል አስረዱ፡፡

1. መሠረታዊ አቅጣጫዎች ምንድን ናቸው?
2. የምንኖርበትን ወረዳ ከሌሎች ወረዳዎች እንዴት ለይቶ ማወቅ ይቻላል?

መሰረታዊ አቅጣጫዎች አራት ናቸው፡፡ እነርሱም ሰሜንና ደቡብ ፤ ምስራቅና ምዕራብ በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህን መሰረታዊ አቅጣቻዎች በመጠቀም የወረዳችንን አንፃራዊ መገኛ በቀላሉ ማመልከት ወይንም ማወቅ እንችላለን፡፡ ምስራቅ የምንለው ፀሐይ የምትወጣበት አቅጣጫ ሲሆን ምዕራብ ደግሞ ፀሐይ የምትጠልቅበት አቅጣጫ ነው፡፡





ሥዕል 1.5 አራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## ተግባር 1.1

ከታች ሥዕል 1.6 እንደተመለከተው ፊታችሁን ወደ ፀሐይ መውጫ አዙራችሁ በመቆም እጆቻችሁን ወደ ጎንና ጎን ዘርጉ



ሥዕል 1.6 መሠረታዊ አቅጣጫዎች


ከላይ በተመለከተው ሥዕል 1.6 መሠረት

ግራ እጃችሁ________________________ያመለክታል።

ቀኝ እጃችሁ________________________ያመለክታል።

ፊታችሁ____________________________ያመለክታል።

ጀርባችሁ___________________________ያመለክታል።




ሥዕል 1.7 የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማዎች እና ወረዳዎች መገኛ

## የግል ስራ 1

ከላይ በሥዕል 1.7 ያለውን ካርታ በትኩረት ተመልክታችሁ የምትገኙበትን ወረዳ አንጻራዊ መገኛን ግለጹ፡፡

የምትገኙበት ወረዳ____________________ነው፡፡

በሰሜን ወረዳ________________________ያዋስነዋል፡፡

በደቡብ ወረዳ________________________ያዋስነዋል፡፡

በምሥራቅ ወረዳ______________________ያዋስነዋል፡፡

በምዕራብ ወረዳ______________________ያዋስነዋል፡፡

**መልመጃ 1.3**

**ሀ. ሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. የወረዳችሁን ንድፍ ካርታ ሥሩ፡፡
2. የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ ለይታችሁ ጻፉ፡፡

## 1.4. በወረዳችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች**

**ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- በወረዳችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን መገኛ በንድፍ ካርታ ታመለክታላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚገኙ መንደሮችን በማመልከት ስማቸውን ትዘረዝራላችሁ፡፡

**ተማሪዎች! በእናንተ ወረዳ ምን ምን ዋና ቦታዎች ይገኛሉ?**

በአዲስ አበባ ውስጥ በአብዛኛው በእያንዳንዱ ወረዳ መገኛ ብዙ የተለያዩ ዋና ዋና ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡- ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ሱቆች፣ ፖሊስ ጣቢያና የመሣሠሉት ናቸው፡፡


## ተግባር 1.2

ዓላማ:- በወረዳችሁ የሚገኙትን ቦታዎች መገኛ ንድፍ ካርታ ማመልከት

መመሪያ:- የቤታችሁን፣ የትምህርት ቤታችሁንና የወረዳችሁን መገኛ የሚያሳይ ንድፍ ካርታ ሥሩ።

1. ወላጆቻችሁን በመጠየቅ በወረዳችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን መገኛ የሚያሳይ ቀላል ንድፍ ካርታ ወይም ስዕል በመስራት ለክፍል መምህራችሁ አሳዩ።
2. በሰራችሁት ቀላል ንድፍ ካርታ ላይ በወረዳችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን ስም በደብተራችሁ ፃፉ።

### መልመጃ 1.4




ሥዕል 1.8 በወረዳ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች

**ሀ. ሥዕል 1.8ን በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. ጤና ጣቢያው የሚገኘው በየትኛው አቅጣጫ ነው?
2. ትምህርት ቤቱ የሚገኘው በየትኛው አቅጣጫ ነው?
3. ፖሊስ ጣቢያው የሚገኘው በየትኛው አቅጣጫ ነው?

## 1.5 የወረዳችን አዋሳኝ ወረዳዎች መገኛና ስማቸው

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የወረዳችሁን አዋሳኝ ወረዳዎች ትዘረዝራላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃል**

- ☞ አዋሣኝ ወረዳ

ተማሪዎች አዋሣኝ ወረዳ ምን ማለት ነው?

አዋሣኝ ወረዳ ከምንኖርበት ወረዳ ጋር ተያያዥ የሆነ ወረዳ ማለት ነው፡፡

**የቡድን ውይይት 1.3**

ሥዕል 1.7ን መሠረት በማድረግ የወረዳችሁን አዋሳኝ ወረዳዎች መገኛና ስም በቡድን ተወያይታችሁ በመዘርዘር መልሱን ለመምህራችሁ አሣዩ፡፡

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

- መገኛ ማለት አንድ ነገር የት እንዳለ ወይም እንደሚገኝ የሚያሳይ ሥፍራ ነው፡፡
- አቅጣጫ ማለት አንድን ቦታ ለመጠቆም ወይም ለማመልከት የምንጠቀምበት መንገድ ነው፡፡
- አንጻራዊ መገኛ ማለት የአንድን ነገር ወይም ቦታ መገኛ በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች ነገሮች ጋር በማነጻፀር የሚያመለክት መግለጫ ነው ፡፡
- አራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች የሚባሉት ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ናቸው፡፡
- ምሥራቅ ፀሐይ የምትወጣበት አቅጣጫ ነው፡፡
- ምዕራብ ፀሐይ የምትጠልቅበት አቅጣጫ ነው፡፡
- አዋሣኝ ወረዳ ከምንኖርበት ወረዳ ጋር ተያያዥ የሆነ ወረዳ ነው፡፡

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል የሆነውን ዓረፍተ ነገር "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. አንድ ቦታ የት እንደሚገኝ የምናሳይበት ዘዴ መገኛ ይባላል::
2. አንድ ቦታ ከሌሎች ቦታዎች አንጻር የት እንደሚገኝ በማነጻፀር የምናመለክትበት መንገድ አንጻራዊ መገኛ ይባላል::
3. ፀሐይ የምትጠልቅበት አቅጣጫ ምሥራቅ ነው::

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ ::**

1. አቅጣጫ አመልካች ስያሜ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ጀርባ ለ. ጎን ሐ. በስተግራ መ. ሁሉም
2. የአንድን ቦታ አንጻራዊ መገኛ ለመግለፅ የምንጠቀምበት መንገድ የትኛው ነው?
   ሀ. ተራራ ለ. ወንዝ ሐ. ሕንፃዎች መ. ሁሉም
3. አበበ ከአልማዝ በስተግራ ቢገኝ አልማዝ ከአበበ በየት በኩል ትገኛለች?
   ሀ. በስተጀርባ ለ. በስተኋላ ሐ. በስተቀኝ መ. በስተግራ
4. መሠረታዊ አቅጣጫዎች ስንት ናቸው?
   ሀ. ሦስት ለ. አራት ሐ. ሁለት መ. አምስት
5. ከሚከተሉት መካከል ፀሐይ የምትወጣበት አቅጣጫ የቱ ነው ?
   ሀ. ደቡብ ለ. ምሥራቅ ሐ. ምዕራብ መ. ሰሜን

## ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ ፡፡

1. መገኛ ማለት ምን ማለት ነው?
2. መሠረታዊ አቅጣጫዎችን ዘርዝሩ፡፡
3. የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ ግለፁ፡፡

## ፍተሻ

ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለፅ የ "✓" ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ፡፡

1. የመገኛ ምንነትን እገልፃለሁ፡፡ ☐
2. የአንጻራዊ መገኛን ምንነትን እገልፃለሁ፡፡ ☐
3. የምኖርበትን ወረዳ አንጻራዊ መገኛ አመለክታለሁ፡፡ ☐
4. የምኖርበትን ወረዳ መገኛ ከአጎራባች ወረዳዎች አንጻር በንድፍ ካርታ ላይ አሳያለሁ፡፡ ☐
5. በወረዳዬ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን መገኛ በንድፍ ካርታ አመለክታለሁ፡፡ ☐
6. በወረዳዬ የሚገኙትን መንደሮችን በማመልከት ስማቸዉን እዘረዝራለሁ፡፡ ☐
7. የወረዳዬን አዋሳኝ ወረዳዎች ሥም እዘረዝራለሁ፡፡ ☐

# ምዕራፍ ሁለት
# ሳይንስን መገንዘብ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ተግባር ትለያላችሁ፡፡
- የስሜት አካላትን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የስሜት አካላትን ተግባር ትለያላችሁ፡፡
- የቁሶችን አካላዊ ባህርያት ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የብርሃን ምንጮችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የብርሃን ባህርያትን በመዘርዘር ታብራራላችሁ፡፡

## የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

2.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችና የስሜት አካላት

2.2 የቁሶች አካላዊ ባህርያት

2.3 የብርሃን ምንጮችና ባህርያት

# 2.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችና የስሜት አካላት

## ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ተግባር ትለያላችሁ፡፡
- የስሜት አካላትን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የስሜት አካላትን ተግባር ትለያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**


- ☞ ውጫዊ የሰውነት ክፍል
- ☞ የስሜት አካላት

# ሀ. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

ተማሪዎች! በአንደኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርታችሁ ስለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ምንነት የተማራችሁትን በማስታወስ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**ተግባር 2.1**

1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችሁን በመጠቀም ስማቸውንና ተግባራቸውን አጠገባችሁ ላሉ ተማሪዎች ተናገሩ።




ሥዕል 2.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

# ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚባሉት ፡-

- ጆሮ
- አፍንጫ
- ፀጉር
- ደረት
- እጅ
- ትከሻ
- ዓይን
- አፍና
- እግር
- ጉልበት
- ራስና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

# ለ. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ተግባር

ሠንጠረዥ 1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ተግባር

| ተ.ቁ | ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች | ተግባር ወይም ጠቀሜታ |
|---|---|---|
| 1 | እጅ | ለመብላት፣ ለመጻፍ፣ እቃ ለማንሳት |
| 2 | እግር | ለመራመድ |
| 3 | ጆሮ | ለመስማት |
| 4 | ዓይን | ለማየት |
| 5 | ፀጉር | ራስን ለመሸፈን |
| 6 | አፍንጫ | ለማሽተት ፣ለመተንፈስ |
| 7 | አፍ | ለመናገር፣ምግብ ለማኘክ |
| 8 | ቆዳ | ሙቀትና ቅዝቃዜን ፣ሸካራነትንና ለስላሳነትን ለመለየት |

## መልመጃ 2.1


**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆነ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. አንገት ውጫዊ የሰውነት ክፍል ነው፡፡
2. አፍ ማሽተት ይጠቅማል፡፡
3. ሙቀትና ቅዝቃዜን በዓይናችን እንለያለን፡፡
4. አፍንጫ ለመተንፈስ ያገለግላል፡፡

**ለ. በ “ሀ” ስር የሚገኙትን ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች በ “ለ” ስር ከተዘረዘሩት ተግባራት ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እግር | ሀ. ለመብላት |
| 2. እጅ | ለ. ራስን ለመሸፈን |
| 3. ፀጉር | ሐ. ለመራመድ |


**ሐ. ከዚህ በታች ያለውን ምስል በመመልከት በቁጥር የተመለከቱትን የሰውነት ክፍሎች ስም ፃፉ ።**



Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## ሐ. የስሜት አካላት



ሥዕል 2.2 የስሜት አካላት

የስሜት አካላት አምስት ናቸው። እነርሱም፡-

1. ዓይን
2. ጆሮ
3. ምላስ
4. አፍንጫ እና
5. ቆዳ ናቸው።

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## መ. የስሜት አካላትና ተግባራት




ሥዕል 2.3 የስሜት አካላት ተግባራት

ሠንጠረዥ 2 የስሜት አካላት ተግባራት

| የስሜት አካላት | ተግባር |
|---|---|
| ዓይን | ለማየት |
| አፍንጫ | ለማሽተት |
| ጆሮ | ለመስማት |
| ቆዳ | ሙቀትና ቅዝቃዜን ለመለየት፣ለመዳሰስ |
| ምላስ | ለመቅመስ ወይም ጣዕምን ለመለየት ፣ ለመናገር |

## መልመጃ 2.2

**ሀ. በ “ሀ” ስር የተዘረዘሩትን የስሜት አካላት በ “ለ” ስር ከተዘረዘሩት ተግባራቸው ጋር በማዛመድ መልሳችሁን በደብተራችሁ ፃፉ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አፍንጫ | ሀ. ለመስማት |
| 2. ምላስ | ለ. ሙቀትን ለመለየት |
| 3. ዓይን | ሐ. ለመቅመስ |
| 4. ጆሮ | መ. ለማሽተት |
| 5. ቆዳ | ሠ. ለማየት |

**ለ. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. የስሜት አካላት ስንት ናቸው?

   ሀ. ሦስት ለ. አራት ሐ. አምስት መ. ስድስት

2. የአንድን ነገር መራራነት ወይም ኮምጣጣነት ለማወቅ የሚጠቀመን የስሜት አካል የትኛው ነው?

   ሀ.ምላስ ለ. ዓይን ሐ. ጆሮ መ. አፍንጫ

3. ድምፅን ለመለየት የሚጠቀመን የስሜት አካል የቱ ነው?

   ሀ. ቆዳ ለ. ጆሮ ሐ. ምላስ መ. ዓይን

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. የስሜት አካላትን ዘርዝሩ።
2. አንድ ነገር ሸካራ ወይም ለስላሳ መሆኑን ለመለየት የሚያገለግለን የስሜት አካል ምን ይባላል?
3. ምላስ ለምን ይጠቅማል?

## 2.2 የቁሶች አካላዊ ባህርያት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የቁስ አካልን ምንነት ትገልጻላችሁ።
- የቁሶችን አካላዊ ባህርያት ትዘረዝራላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

☞ ቁስ አካል ☞ አካላዊ ባህርይ ☞ መጠነ ቁስ

## ቁስ አካል ምንድን ነው?




ሥዕል 2.4 የተለያዩ ቁሶች

ቁስ አካል ማለት ማንኛውም ቦታ የሚዝና የራሱ ክብደት ያለው ነገር ነው:: ሁሉም ቁሶች የራሳቸው የሆነ ክብደት አላቸው::

ለምሳሌ:-

- አየር
- ውኃ
- እርሳስ
- ወተት
- ስኳር
- መዳብ
- መፅሐፍ
- መስታወት
- ወርቅ
- ደብተር
- ብዕር
- ብረት
- ጨው እና የመሳሰሉት የቁስ አካል ምሳሌዎች ናቸው::

## • የቁስ አካል አካላዊ ባህርያት ምንድን ናቸው?

የቁስ አካል አካላዊ ባህርያት ማለት የአካባቢው መጠነ ሙቀትና የከባቢ አየር ግፊት ቋሚ ሆነው ቁስ አካሉ ስሪቱን ሳይቀይር የሚያሳያቸው ባህርያት ናቸው፡፡ የቁስ አካል አካላዊ ባህርያት ማለት አንድ ቁስ አካል ስሪቱን ሳይቀይር የሚያሳያቸው ባህርያት የቁስ አካል አካላዊ ባህርያት ይባላሉ፡፡ የቁሶች የተወሰኑ አካላዊ ባህርያት በቀላሉ በስሜት አካላት ሊለዩ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ቀለም፣ ቅርፅ እና ጣዕም

የቁሶች አካላዊ ባህርያት የሚባሉት ፡-

- ቀለም
- ብርሃን አሳላፊነት
- አካላዊ ሁነት
- ብርሃን ዘጊነት
- እፍግታ
- ቅርፅ
- ጣዕም
- ተለጣጭነት
- ተሰባሪነት
- ተጠመዝማዥነትና

የመሳሰሉት ናቸው ፡፡

መልመጃ 2.3

ሀ. ከዚህ በታች ባለው በሣጥን ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላት ወይም ሐረጎች በመምረጥ ባዶ ቦታውን በተገቢው ቃል ወይም ሐረግ በመሙላት መልሱ፡፡

| መጠነ ቁስ | |
|---|---|
| አካላዊ ባህርይ | ቀለም |
| ጣዕም | ቁስ አካል |

1. ቦታ የሚይዝና መጠነ ቁስ ያለው ማንኛውም ነገር_ ይባላል::
2. ቁሶች ስሪታቸውን ሳይቀይሩ የሚያሳዩት ባህርይ____ይባላል::
3. በማየት የሚለይ አካላዊ ባህርይ________________ነው::
4. በመቅመስ የሚለይ አካላዊ ባህርይ______________ነው::
5. በአንድ አካል ውስጥ የሚገኝ የቁስ መጠን__________ይባላል::


## ሀ. ተጠመዝማዥነት፣ ተጠፍጣፊነት፣ ተሰባሪነት እና ተለጣጭነት

የቁሶች የመጠምዘዝና ወደ ቀጭን ሽቦነት የመለወጥ አካላዊ ባህርይ ተጠመዝማዥነት ይባላል::



ሥዕል 2.5 የቁሶች ተጠመዝማዥነት


ተጠፍጣፊነት የቁሶች በመቀጥቀጥ ወደ ጠፍጣፋ ቅርፅ የመለወጥ አካላዊ ባህርይ ነው ።



ሥዕል 2.6 የቁሶች ተጠፍጣፊነት

ለምሳሌ፡- አልሙኒየም፣ መዳብ፣ ብረት፣ ወርቅ፣ ብርና የመሳሰሉት ተጠመዝማዥና ተጠፍጣፊ ቁሶች ናቸው፡፡

ተሰባሪ ቁሶች የምንላቸው ተለጣጭና ተጠፍጣፊ ያልሆኑ ቁሶችን ሲሆን አምፖል፣ ጡብ፣ ብሎኬት፣ ብርጭቆ፣ ግራፋይት፣ ድንጋይ፣ ድኝ፣ ከሰል፣ ጠርሙስ፣ በረዶና የመሳሰሉት የተሰባሪ ቁሶች ምሳሌዎች ናቸው፡፡







ምሥል 2.7 ተሰባሪ ቁሶች

የቁሶች የመለጠጥና የመተጣጠፍ ችሎታ ተለጣጭነት ይባላል፡፡ ለምሳሌ፡- የብር ላስቲክ፣ ፊኛና ከላስቲክ ከተሰራ ፀጉር ማስያዣ ተለጣጭ ቁሶች ናቸው፡፡




ሥዕል 2.8 የቁሶች ተለጣጭነት

## ለ. ብርሃን አሳላፊነት እና ብርሃን ዘጊነት

ብርሃን ሙሉ በሙሉ በውስጣቸው የሚያሳልፉ ቁሶች ብርሃን አሳላፊ ቁሶች ይባላሉ። ቁሶች ብርሃንን ሙሉ በሙሉ በውስጣቸው የማሳለፍ ባህርይ ደግሞ ብርሃን አሳላፊነት ይባላል።




ሥዕል 2.9 ብርሃን አሳላፊነት

ብርሃን አሳላፊ ከሆኑ ቁሶች ውስጥ መስታወት፣ አየር፣ ንፁህ ውኃ፣ ምስሪት፣ ቀለም የሌለው ንፁህ ፕላስቲክና ቀለም የሌለው ንፁህ ብርጭቆን መጥቀስ ይቻላል።







ምስል 2.10 ብርሃን አሳላፊ ቁሶች


ብርሃን ሙሉ በሙሉ በውስጣቸው የማያሳልፉ ቁሶች ብርሃን ዘጊ ተብለው ይታወቃሉ። የቁሶች ብርሃንን ሙሉ በሙሉ በውስጣቸው ያለማሳለፍ ባህርይ ብርሃን ዘጊነት ይባላል።




ምስል 2.11 ብርሃን ዘጊነት

ለምሳሌ ፦ ድንጋይ፣ መፅሐፍና ግድግዳ።





ምስል 2.12 ብርሃን ዘጊ ቁሶች

## መልመጃ 2.4

**ሀ. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. ቁስ አካል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ውኃ ለ. ስኳር ሐ. መዳብ መ. ሁሉም

2. ተጠፍጣፊ ያልሆነው ቁስ የቱ ነው?

   ሀ. ድኝ ለ. ወርቅ ሐ. ብረት መ. መዳብ

3. ተለጣጭ የሆነው ቁስ የቱ ነው?

   ሀ. የፀጉር ማስያዣ ሐ. የእጅ ላስቲክ

   ለ. ፊኛ መ. ሁሉም

4. ብርሃን አሳላፊ ያልሆነው ቁስ የትኛው ነው?

   ሀ. ድንጋይ ለ. ምስሪት ሐ. መስታወት መ. አየር

5. ብርሃን ዘጊ የሆነው ቁስ የትኛው ነው?

   ሀ. ንፁህ ውኃ ለ. ግድግዳ ሐ. ድንጋይ መ. ለ እና ሐ

6. የቁሶች ወደ ሽቦነት የመለወጥ አካላዊ ባህርይ ምን ይባላል?

   ሀ. ተጠፍጣፊነት ሐ. ተጠመዝማዥነት

   ለ. ተሰባሪነት መ. ብርሃን ዘጊነት

# 2.3 የብርሃን ምንጮችና ባህርያት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡

- የብርሃንን ምንነት ትገልፃላችሁ፡፡
- የብርሃን ምንጮችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ተፈጥሮአዊና ሠው ሰራሽ የብርሃን ምንጮችን ትለያላችሁ፡፡
- የብርሃን ባህርያትን ታብራራላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ብርሃን
- ሠው ሰራሽ የብርሃን ምንጭ
- ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጭ
- የብርሃን ፅብረቃ
- የብርሃን ስብረት


## ሀ. የብርሃን ምንጮች

**የቡድን ውይይት 2.1**

በቡድን ሆናችሁ የብርሃን ምንጮችን ከዘረዘራችሁ በኋላ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ብላችሁ በመመደብ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource







ምስል 2.13 የብርሃን ምንጮች

ብርሃን ነገሮች በዓይን እንዲታዩን የሚያደርግ ሞገድ ነው፡፡

ብርሃን በዓይን የሚታይ የጉልበት አይነት ነው፡፡ የብርሃን ምንጮች ሁለት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

1. ተፈጥሮአዊ እና
2. ሰው ሠራሽ ተብለው ይመደባሉ፡፡

ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጮች የምንላቸው በተፈጥሮ የሚገኙ የብርሃን ምንጮችን ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ፀሐይ፣ ኮከቦች፣ መብረቅና ጨረቃ ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጮች ናቸው፡፡ ፀሐይ ለመሬት ዋና የብርሃን ምንጭ ናት፡፡

ሰው ሠራሽ የብርሃን ምንጮች የሚባሉት በሰው አማካኝነት የሚሰሩ የብርሃን ምንጮች ናቸው፡፡

ለምሳሌ ፡- አምፖል፣ ባትሪ፣ ሻማና እሳት ሰው ሠራሽ የብርሃን ምንጮች ናቸው፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## ለ. የብርሃን ባህርያት

### የቡድን ውይይት 2.2

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡


1. ብርሃን እንዴት ይጓዛል?
2. የሰው ምስል በዝርግ መስታወት ውስጥ እንዴት ይፈጠራል?




3. ቀስተ ደመና እንዴት ይፈጠራል?



ብርሃን በቀጥታ መስመር ይጓዛል፡፡





ምስል 2.14 የብርሃን ቀጤመስመራዊ ጉዞ (ንዛት)

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



የብርሃን ከአንፀባራቂ ነገሮች ላይ ተንፀባርቆ የመመለስ ባህርይ የብርሃን ፅብረቃ ይባላል፡፡ ምስል በዝርግ መስታወት ውስጥ የሚፈጠረው በብርሃን ፅብረቃ አማካኝነት ነው፡፡



ምስል 2.15 የብርሃን ፅብረቃ

ብርሃን ከአንድ ብርሃን አስተላላፊ ቁስ ወደ ሌላ ብርሃን አስተላላፊ ሲጓዝ አቅጫውን ይቀይራል፡፡ ይህ የብርሃን ባህርይ የብርሃን ስብረት ተብሎ ይጠራል:: ለምሳሌ ፡- ቀስተ ደመናና ጥብርብርታ በብርሃን ስብረት አማካኝነት የሚፈጠሩ ክስተቶች ናቸው፡፡



ምስል 2.16 የብርሃን ስብረት ውጤቶች (ክስተቶች)

## ተግባር 2.2

ርዕስ - የብርሃን ስብረት

ዓላማ - የብርሃንን ስብረት በሙከራ ማሳየት

የሚያስፈልጉ ነገሮች ፡- ነጭ ወረቀት፣ ብርጭቆዎች፣ ውኃ፣ ማርከር (ምልክት ማድረጊያ)

የአሰራር ቅደም ተከተል ፡-

1. ነጩ ወረቀት ላይ ሁለት ተመሳሳይ አቅጣጫ ያላቸው ጨረሮችን አንደኛውን ከወረቀቱ ላይኛው ጫፍ ላይ እና አንዱን ደግሞ ከወረቀቱ ታችኛው ጫፍ ላይ በማድረግ ሳሉ።
2. ብርጭቆውን በውኃ በከፊል ወይም በሙሉ ሙሉት
3. ወረቀቱን ውኃ ወደ ያዘው ብርጭቆ የታችኛው ክፍል አስጠጉ።
4. ወረቀቱን ባስጠጋችሁበት የብርጭቆ ክፍል (ጠርዝ) ተቃራኒ ሆናችሁ በብርጭቆው ውስጥ ተመልከቱ።

**ጥያቄ**

1. ምን አስተዋላችሁ?
2. ከተግባሩ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

- እጅ፣ እግር፣ ራስ፣ ትከሻ፣ አንገት፣ ጆሮ፣ አፍንጫ፣ ጉልበት፣ ክርንና የመሳሰሉት ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ናቸው።
- እጅ ለመዳሰስ፣ እግር ለመራመድ፣ ጆሮ ለመስማት፣ አፍንጫ ለማሽተት፣ ይጠቅመናል።
- አምስቱ የስሜት አካላት ዓይን፣ አፍንጫ፣ ጆሮ፣ ቆዳና ምላስ ናቸው።
- ዓይን ለማየት፣ ጆሮ ለመስማት፣ አፍንጫ ለማሽተት፣ ቆዳ ለመዳሰስ፣ ምላስ ለመቅመስ ያገለግላሉ።
- የቁሶች አካላዊ ባህርያት የሚባሉት ብርሃን አሳላፊነት፣ቅርፅ ብርሃን ዘኒነት፣ ቀለም፣ ተሰባሪነት፣ ተለጣጭነት፣ ወዘተ ናቸው።
- መጠነቁስ በአንድ አካል ውስጥ የሚገኝ የቁስ መጠን ነው ።
- ተጠመዝማዥነት የቁሶች የመጠምዘዝና ወደ ሽቦነት የመለወጥ አካላዊ ባህርይ ነው።
- የቁሶች የመለጠጥና የመተጣጠፍ ችሎታ ተለጣጭነት ይባላል።
- የብርሃን ምንጮች ሁለት ናቸው። እነርሱም ፦ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ናቸው።
- ቁሶች ብርሃንን ሙሉ በሙሉ በውስጣቸው የማሳለፍ አካላዊ ባህርይ ብርሃን አሳላፊነት ይባላል።
- ብርሃን ነገሮች በዓይን እንዲታዩን የሚያደርግ ሞገድ ነው።
- የብርሃን ፅብረቃ ብርሃን ከአንፀባራቂ ነገሮች ላይ ነጥሮ የመመለስ ባህርይ ነው።

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. ጉልበትና ክርን ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ናቸው፡፡
2. ቦታ የሚይዝና መጠነ ቁስ ያለው ማንኛውም ነገር ቁስ ይባላል፡፡
3. ቀለም በእጃችን የሚለይ አካላዊ ባህርይ ነው፡፡
4. ብርሃን የሚጓዘው በቀጥታ መስመር ነው፡፡
5. ቀስተ ደመና በብርሃን ስብረት የሚፈጠር የተፈጥሮ ክስተት ነው፡፡

### ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱን በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

1. ውጫዊ የሰውነት ክፍል ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ራስ ለ. እጅ ሐ. ልብ መ. ደረት

2. ሸካራነትንና ለስላሳነትን ለመለየት የሚያገለግለው የስሜት አካል ነው?

   ሀ. ምላስ ለ. ቆዳ ሐ. ዓይን መ. አፍንጫ

3. ቁስ አካል የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. አየር ለ. ወተት ሐ. ጨው መ. ሁሉም

4. የቁሶች አካላዊ ባህርይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ተሰባሪነት ሐ. ብርሃን አሳላፊነት

ለ. ተጠመዝማዥነት መ. ሁሉም

5. ተጠፍጣፊ የሆነው ቁስ የትኛው ነው?

ሀ. ወርቅ ለ. ድንጋይ ሐ. ብርጭቆ መ. አምፖል

6. ብርሃን አሳላፊ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አየር ለ. መስታወት ሐ. ግድግዳ መ. ሀ እና ለ

7. ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጭ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ፀሐይ ለ. ከዋክብት ሐ. መብረቅ መ. ሁሉም

ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ባዶ ቦታውን በተገቢው ቃል ወይም ሐረግ በመሙላት መልሳችሁን በደብተራችሁ ፃፉ።

1. ________ነገሮች በዓይን እንዲታዩን የሚያደርግ የጉልበት ዓይነት ነው።

2. የመሬት ዋና የብርሃን ምንጭ____________ናት።

3. ብርሃን ከአንፀባራቂ ነገሮች ላይ ነጥሮ የመመለስ ባህርይ______________ይባላል።

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## ፍተሻ

ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለፅ የ "✓" ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ።

1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን እዘረዝራለሁ። ☐
2. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ተግባር እለያለሁ። ☐
3. የስሜት አካላትን እዘረዝራለሁ። ☐
4. የስሜት አካላትን ተግባር እለያለሁ። ☐
5. የቁሶችን አካላዊ ባህርያት እዘረዝራለሁ። ☐
6. የብርሃን ምንጮችን እዘረዝራለሁ። ☐
7. የብርሃን ባህርያትን በመዘርዘር አብራራለሁ። ☐

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# ምዕራፍ ሦስት

# ተፈጥሮአዊ አካባቢ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የአየር ሁኔታን ምንነት ትገልጻላችሁ፡፡
- የአየር ሁኔታን ምሳሌዎች ትጠቅሳላችሁ፡፡
- የአየር ንብረት ምንነትን ትገልጻላችሁ፡፡
- የአየር ንብረት በአኗኗር ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ትገልጻላችሁ፡፡
- ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችን ትለያላችሁ፡፡
- በአካባቢያችን በስፋት የሚገኙ ዕፅዋትን ትለያላችሁ፡፡
- ለዕፅዋት ዕድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ትለያላችሁ፡፡
- የዕፅዋትን የተለያዩ ጥቅሞች ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ምግብ የጉልበት ምንጭ መሆኑን ትገልጻላችሁ፡፡
- እንስሳትን (አጥቢዎች፣ ወፎች፣ አሳዎች፣ ገበሎ አስተኔዎችና እንቁራሪት አስተኔዎች) በውጫዊ ገጽታቸው በመዘርዘር ትመድባላችሁ፡፡
- መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉና በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሶችን ትለያላችሁ፡፡
- ከወዳደቁ ነገሮች ሊሠሩ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮችን ትገምታላችሁ፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

3.1. የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት

3.2. በወረዳችን የሚገኙ ዕጽዋት

3.3. በወረዳችን የሚገኙ እንስሳት

3.4. በወረዳችን የሚገኙ ቁሳዊ ሀብቶች

3.5. የወረዳችችንን አካባቢ መንከባከብ

## 3.1. የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የአየር ሁኔታን ምንነት ትገልጻላችሁ፡፡
- የአየር ሁኔታን ምሳሌዎች ትጠቅሳላችሁ፡፡
- የአየር ንብረት ምንነትን ትገልጻላችሁ፡፡
- የአየር ንብረት በአኗኗር ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ትገልጻላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- አየር
- የአየር ሁኔታ
- የአየር ንብረት

ተማሪዎች! ስለ አየር ሁኔታና ስለ አየር ንብረት ምንነት በአንደኛ ክፍል የአካባቢ የሳይንስ ተምራችኋል።

**የማነቃቂያ ጥያቄ:-**

1. የአየር ሁኔታን ምንነት ግለፁ።
2. የአየር ሁኔታ ምሳሌዎችን ዘርዝሩ።
3. የአየር ንብረት በአኗኗር ላይ ያለውን ተጽዕኖ ተናገሩ።

## ሀ. የአየር ሁኔታ

አየር ቀለምና ሽታ የሌለው በዓይን የማይታይ ነገር ግን ቦታ የሚዝና ክብደት ያለው ህይወት ላላቸው ነገሮች አስፈላጊ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ነው። አየርን በአካባቢያች እንደሚገኝ በቀላሉ ማረጋገጥ እንችላለን። ለምሳሌ:- ፊኛ፣ ኳስ፣ ጎማና የመሳሰሉትን ነገሮች በመንፋት አየር መኖሩን እና ቦታ መያዙን በቀላሉ መረጋገጥ ይቻላል።

የአየር ሁኔታ ማለት በየዕለቱ በአንድ አካባቢ የሚታይ የዝናብ፣ የሙቀት፣ የንፋስ ሁኔታንና የመሳሰሉት መግለጫ ነው። የአየር ሁኔታ በአንድ ውስን በሆነ አካባቢ ለአጭር ጊዜ በየዕለቱ የሚከሰተው የአየር ሁኔታ ለውጥ የዕለቱ አየር ሁኔታ በመባል ይታወቃል።

## ለ. የአየር ሁኔታ ምሳሌዎች

የአየር ሁኔታ ምሳሌዎችን ዘርዝሩ።

የአየር ሁኔታ ምሳሌዎች የሚባሉት ፀሐያማ፣ ዝናባማ፣ ነፋሻማ፣ ደረቃማ፣ ሞቃታማና ቀዝቃዛማ ናቸው።



ስዕል 3.1 የአየር ሁኔታ ምሳሌዎች

**የቡድን ውይይት 1**

ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ::

1. ፀሐያማ፣ ዝናባማ፣ ነፋሻማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ የሚያሳየው ከቀረበው ሥዕል 3.1 በመመልከት ለመምህራችሁ አመልክቱ::
2. በወረዳችን ያለው የአየር ሁኔታ ከላይ ከተሰጠው ሥዕል አንፃር ከየትኛው ጋር ይመሳሰላል::

## ሐ. የአየር ንብረት

የአየር ንብረት ምንድን ነው?


የአየር ንብረት በአንድ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የአየር ሁኔታ (የአየር ጠባይ) አማካይ ውጤት ነው:: የአየር ንብረት በአንድ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የተመዘገበ የሙቀት መጠን፣ የዝናብ መጠን፣ የአየር እርጥበት፣ የንፋስ ፍጥነትና የመሳሰሉትን መረጃዎች በማስላት የሚገኝ አማካይ ውጤት ነው:: በዚህም መሠረት እርጥበታማ የአየር ንብረት፣ ደረቃማ የአየር ንብረት፣ ቀዝቃዛማ የአየር ንብረት፣ ሞቃታማ የአየር ንብረት በማለት ስለ አየር ንብረት መግለጽ ይቻላል::

ለምሳሌ፡- የአዲስ አበባ ከተማ የአየር ንብረት በበጋ ደረቅና ሞቃታማ ሲሆን በክረምት ደግሞ ዝናባማና ቀዝቃዛማ ነው::

## የቡድን ውይይት 2


የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ከተወያያታችሁ በኋላ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅረቡ።

1. የአየር ንብረት ምንድ ነው?
2. የወረዳችሁን የአየር ንብረት በፅሁፍ አስረዱ።









ሥዕል 3.2 የአየር ንብረት (በረሃማ ፣ ቀዝቃዛማ ፣ ዝናባማ)

# ወቅቶች

በአገራችን ኢትዮጵያ አራት ወቅቶች አሉ:: እነርሱም:- ፀደይ (ጥቢ)፣ ክረምት፣ በጋና በልግ ናቸው::

በኢትዮጵያ ለምሳሌ:- ሰኔ፣ ሀምሌና ነሐሴ የክረምት ወራት፤ መስከረም፣ ጥቅምትና ህዳር የፀደይ ወቅት፤ ታህሳስ፣ ጥርና የካቲት የበጋ ወራት፤ መጋቢት፣ ሚያዝያና ግንቦት የበልግ ወራት ናቸው::

## ተግባር 1 የቡድን ስራ

በቡድን በመሆን ከዚህ በታች በቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ በጽሁፍ አቅርቡ::

1. በወረዳችሁ ዋና ዋና ዝናባማ ወራትን የሚያመለክት ጥርብ ግራፍ ተጠቅማችሁ በወረዳችሁ የትኞቹ ወራቶች ከፍተኛ ዝናብ እንደሚዘንብ ለመምህራችሁ አመልክቱ::
2. በክረምትና በበጋ መካከል ያለውን ልዩነት ግለፁ::

ክረምት የሚባለው ወቅተ በአብዛኛው ዝናባማና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ ያለው ሲሆን በጋ ደግሞ ሞቃትና ደረቅ የአየር ሁኔታ አለው:: እንዲሁም ፀደይ የምንለው ነፋሻማና እርጥበት የሚበዛበት የአበባ ወቅት ሲሆን፤ በልግ ደግሞ ሞቃታማና እርጥበታማ የአየር ሁኔታ ያለው ወቅት ነው::

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource





ሥዕል 3.3 ፀሐያማ እና ዝናባማ ፣ ነፋሻማና ደረቃማ

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## መ. የአየር ንብረት በአኗኗር ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ

የአንድ አካባቢ አየር ንብረት በሰዎች አኗኗር፣ እንቅስቃሴ፣ አመጋገብና የአለባበስ ሁኔታ ላይ የተለያዩ ተጽዕኖዎችን ያሳድራል፡፡

**የቡድን ውይይት 3**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ከተወያያታችሁ በኋላ መልሳችሁን ለመምህራችሁ አቅረቡ፡፡

1. የአየር ንብረት በአኗኗር ላይ የሚያሳድረውን ተፅፅኖ ዘርዝሩ፡፡
2. የአየር ንብረት በአለባበስና በገዞ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ግለፁ፡፡

**የአየር ንብረት በአመጋገብ ላይ ያለው ተጽዕኖ፡-** ምግቦች እንደ የአየር ንብረቱ ሁኔታ ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ብርዳማ በሆኑ አካባቢዎች ከፍተኛ ሙቀት ሰጪ ምግቦች እንደ ዳቦ ፣ ድንች፣ ማርና ገንፎ የመሳሰሉትን ምግቦች መመገብ ያስፈልጋል፡፡

**የአየር ንብረት በአለባበስ ላይ ያለው ተጽዕኖ፡-** ሰዎች እራሣቸውን ከቅዝቃዜና ከከፍተኛ ሙቀት ለመከላከልና ሰውነታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙባቸው የልብስ አይነቶች እንደ አየር ንብረቱ ሁኔታ የተለያዩ ናቸው፡፡ ለምሣሌ፡- ብርዳማ በሆኑ አካባቢዎች ያለውን ቅዝቃዜ ለመቋቋም ከሱፍ፣ ከጥጥ እና ከቆዳ የተሰሩ ልብሶችን ይለብሳሉ፡፡ በቆላማና በረሃማ አካባቢዎች ከፍተኛ ሙቀት ባለባቸው አካባቢዎች ቀለል ያሉ ከጥጥና ሐር የተሰሩ ልብሶችን መልበስ ያስፈልጋል፡፡

**የአየር ንብረት በእንቅስቃሴ ላይ ያለው ተጽዕኖ:-** ሰዎች ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ጊዜ እንደ አየር ንብረቱ ይወሰናል፡፡






ምስል 3.4 የአየር ንብረት በአለባበስ ላይ ያለው ተጽዕኖ

## ሠ. የአየር ንብረት ለውጥና የሰው ተጽዕኖ

የአየር ንብረት ለውጥ የሚከሰተው ወደ አየር በሚለቀቅ ጭስ አማካኝነት ነው፡፡ ለአየር ንብረት መለወጥ ዋና ዋና ምክንያቶች የደን መጨፍጨፍና የደን ቃጠሎ፤ ከተሽከርካሪዎችና ከኢንደስትሪዎች የሚለቀቀው ጭስ ለአየር ንብረት ለውጥ ዋና ምክንያቶች ናቸው፡፡ ሰው በተፈጥሮ አካባቢያችን ላይ ብዙ የተለያዩ ተጽዕኖ ያሳደራል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ የሚከሰተው በተፈጥሮዊ ክስተትና በሰው ተጽዕኖ ነው፡፡





ምስል 3.5 የደን ጭፍጨፋ፣ቃጠሎና የፋብሪካ ጭስ

## የቡድን ውይይት 4

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ከተወያያታችሁ በኋላ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

1. በወረዳችሁ የአየር ንብረት ለውጥ ፍጥነትና ተፅዕኖ ግለፁ።
2. የአየር ንብረት እየተለወጠ ስለመሆኑ እንዴት ማወቅ ይቻላል?

የአየር ንብረት ለውጥ የሙቀት መጨመር፣ የዝናብ እጥረት፣ ድርቅና ጎርፍ ያስከትላል። የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ዕፅዋትን መትከልና መንከባከብ፣ እንስሳትንና ፓርኮችን መጠበቅ፣ ቆሻሻን በየቦታው ከማቃጠል መቆጠብ ያስፈልጋል።

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## ተግባር 2 የቡድን ስራ

ዓላማ፡- በአየር ንብረት ላይ የሰው ተጽዕኖን መገንዘብ፡፡

1. በአየር ንብረት ላይ የሰው ልጅ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለመምህራችሁ ግለጹ::

2. በወረዳችሁ የአየር ንብረት ለውጥ እንዳይከሰት ምን መደረግ አለበት? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## መልመጃ 3.1

ሀ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት " ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሀሰት " በማለት መልሱ፡፡

1. ፀሐይማ፣ ዝናባማና ደረቃማ የአየር ሁኔታ ምሳሌዎች ናቸው፡፡
2. የአየር ንብረት በአኗኗር ላይ ተፅፅኖ የለውም፡፡
3. የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነት የላቸውም፡፡
4. ክረምት ቀዝቃዛና ዝናባማ ወራት ነው፡፡

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጣችሁ አማራጭ መልሶች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት አንዱ የአየር ሁኔታን ያመለክታል፡፡

   ሀ. ዝናባማ ለ. ነፋሻማ ሐ. ሞቃታማ መ. ሁሉም

2. ለአየር ንብረት መለወጥ ምክንያት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ከኢንዱስትሪዎች የሚወጣ ጭስ ሐ. ዛፎችን መትከል

   ለ. ደንን መጨፍጨፍ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3.ከሚከተሉት የአየር ሁኔታ ምሳሌ የሆነው የቱ ነው?
ሀ. ዝናባማ ለ. ፀሐያማ ሐ. ደረቃማ መ. ሁሉም

**ሐ. የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በተስማሚው ቃላት ወይም ሀረጋት አሟሉ፡፡**

1.______________በአንድ አካባቢ የሚኖር ዕለታዊ የዝናብ፣ የሙቀትና የንፋስ ሁኔታ የሚያሳይ ነው፡፡

2.___________ነፋሻማና እርጥበት ያለበት ወቅት ነው፡፡

**መ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ ፡፡**

1.የአየር ንብረት ምንነት ግለፁ፡፡

2.የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነት አብራሩ፡፡

3.በወረዳችሁ ዋና ዋና ዝናባማ ወራትን ጥርብ ግራፍ ሰርታችሁ አመልክቱ፡፡

4.የአየር ንበረት በአኗኗር ላይ ያለውን ተፅጽኖ ግለጹ፡፡

## 3.2. በወረዳችን የሚገኙ ዕፅዋት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- በወረዳችን በስፋት የሚገኙ ዕፅዋትን ትገልፃላችሁ፡፡
- ለዕፅዋት ዕድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ትለያላችሁ፡፡
- የዕፅዋትን የተለያዩ ጥቅሞች ትዘረዝራላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ዕፅዋት
- ዝርያዎች
- መመናመን

**የማነቃቂያ ጥያቄ**


1. በወረዳችን በስፋት የሚገኙ ዕፅዋትን ስም ተናገሩ።
2. ለዕፅዋት ዕድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዘርዝሩ።
3. በወረዳችን የሚገኙ ዕፅዋትን ጠቀሜታ ግለፁ።

ዕፅዋት ሕይወት ያላቸው፣ ከቦታ ቦታ የማይንቀሳቀሱ፣ አየር የሚተነፍሱ፣ የራሳቸውን ምግብ የሚያዘጋጁ፣ የሚራቡና የሚያድጉ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው። ዕፅዋት በመጠናቸው፣ በግንዳቸው ቅርፅ፣ በቅጠላቸው ቅርፅና መጠን ይለያያሉ። በአካባቢያችን የሚገኙ ዕፅዋትን የተለያዩ መስፈርቶች በማውጣት መመደብ ይቻላል።

## ሀ. የዕፅዋት አካል ክፍሎችና ተግባራቸው

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

የዕፅዋት ዋና ዋና አካል ክፍሎች ዘርዝሩ።




ምስል 3.6 የዕፅዋት ክፍሎች

## የግል ስራ 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::

1. የዕፅዋት አካል ክፍልችን ሳሉና ስማቸውን ፃፉ::

2. የዕፅዋት ሥር፣ ግንድና ቅጠል ልዩነት ግለፁ::


የዕፅዋት አካል ክፍሎች በመጠናቸውና በቅርፃቸው እንዲሁም በተግባራቸው ይለያያሉ:: ዕፅዋት የተለያዩ የአካል ክፍሎች አሏቸው:: እንርሱም:- ግንድ፣ ቅጠል፣ ስርና አበባ ናቸው:: ከመሬት በላይ የሚገኙት የዕፅዋት አካል ክፍሎች ግንድ፣ ቅጠልና አበባ ሲሆኑ ስር ከመሬት በታች የሚገኝ የዕፅዋት አካል ክፍል ነው::

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# ቅጠልና ተግባሩ

ቅጠል በአብዛኛው አረንጓዴ ቀለም ያለው የዕፅዋት አካል ክፍል ነው፡፡ ዋና ተግባሩም ለዕፅዋቱ ምግብ ማዘጋጀት ነው፡፡



ስዕል 3.7 የተለያዩ ቅጠሎች

# ግንድና ተግባሩ


ግንድ የተዘጋጀ ምግብ ከቅጠሎች ወደ ሌሎች የዕፅዋት ክፍሎች ያስተላልፋል፤ ውሃና ማዕድናትን ወደ ቅጠሎችና ቅርንጫፎች ያደርሳል፣ የዕፅዋቱን ቅጠሎችና ቅርንጫፎች ይሸከማል፤ እንዲሁም የአንዳንድ ዕፅዋት ግንዶች ለምግብ ማከማቻነት ያገለግላሉ፡፡



ምስል 3.8 የተለያዩ የግንድ አይነት

## ሥርና ተግባሩ

ውሃና ማዕድናት ወደ ግንድ ያስተላልፋል፤ ለአንዳንድ ዕፅዋት በምግብ ማከማቻነትና ዕጽዋት እንዲቆሙ ከመሬት ጋር አጣብቆ ለመያዝ ያገለግላል፡፡



ሥዕል 3.9 የተለያዩ ስሮች

**አበባ ተግባሩ፡-** አበቦች በቅርፃቸው፣ በመጠናቸው፣ በቀለማቸውና በሽታቸው ይለያያሉ፡፡አንዳንድ ዕፅዋት አበባ የላቸውም፡፡

አበቦች የዕፅዋት የመራቢያ ክፍሎች እንዲሁም ዘርና ፍሬ የሚፈጠሩባቸው የዕፅዋት ክፍሎች ናቸው፡፡



ሥዕል 3.10 የተለያዩ አበባ አይነት

# ለ. በአካባቢያችን የሚገኙ ዕፅዋትን መመደብ

በአካባቢያችን የሚገኙ ዕፅዋትን የተለያዩ መስፈርቶች በማውጣት መመደብ ይቻላል፡፡ ዕፅዋት መጠናቸውን መሰረት በማድረግ በሶስት ይመደባሉ፡፡ እነርሱም:- ትናንሽ ዕፅዋት፣ መካከለኛ ዕፅዋት (ቁጥቋጦ)፣ ትላልቅ ዕፅዋት (ዛፍ)

## ትናንሽ ዕፅዋት፡-

ሳሮችና ሌሎች አነስተኛ ዕፅዋትን ያጠቃልላል፡፡



ምስል 3.11 ትናንሽ ዕፅዋትን

## መካከለኛ ዕፅዋት/ቁጥቋጦዎች:-

መካከለኛ መጠን ያላቸው የዕፀዋት አይነቶች ናቸው፡፡



ምስል 3.12 መካከለኛ ዕፅዋት

## ትላልቅ ዕፅዋት (ዛፎች) :-

ከሌሎቹ አንፃር ሲታዩ በጣም ትላልቅ ናቸው::




ምስል 3.13 ትላልቅ ዕፅዋት (ዛፎች)

## ለዕፅዋት ዕድገት የሚያስፈልጉ ነገሮች

*የማነቃቂያ ጥያቄ*

*ዕፅዋት ለማደግ ምን ምን ያስፈልጋቸዋል?*

ለዕፅዋት እድገት የሚያስፈለልጉ ዋና ዋና ነገሮች አየር፣ አፈር፣ ውሃና የፀሐይ ብርሃን ናቸው። ዕፅዋት ለዕድገታቸው አስፈላጊ የሆኑ ማዕድናትን ከአፈር ያገኛሉ። ዕፅዋት ምግባቸውን ለማዘጋጀት ከሚያስፈልጋቸው ነገሮች ውስጥ ውሃ አንዱ ነው። ዕፅዋት ምግባቸውን ለማዘጋጀት እንዲሁም ያዘጋጁትን ምግብ ለመጠቀም አየር ያስፈልጋቸዋል።

## የቡድን ውይይት 5

ሦስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1. ለዕፅዋት ዕድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዘርዝሩ።
2. ዕፅዋት የፀሐይ ብርሐንና አየር ባያገኙ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

# የዕፅዋት ጠቀሜታ

## የማነቃቂያ ጥያቄ

1. የዕፅዋት ጥቅሞችን ዘርዝሩ።
2. በወረዳችሁ ሚገኙ ዕፅዋትን ጠቀሜታ ግለፁ።

ዕፅዋት በርካታ ጠቀሜታ አላቸው። ለምሳሌ፡- ዕፅዋት ለምግብነት፣ ለዱር እንስሳት መጠለያነት፣ አካባቢን ለማስዋብ፣ መድኃኒት ለማዘጋጀትና የተለያዩ የቤት ዕቃዎችን ለመስራት ያገለግላሉ።



Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource





ምስል 3.14 የዕፅዋት ጠቀሜታ

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## መልመጃ 3.2.

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሀሰት" በማለት መልሱ።**

1. ዕፅዋት ምግባቸውን የሚያዘጋጁት በቅጠላቸው ነው።
2. ስር ከመሬት በላይ የሚገኝ የዕፅዋት አካል ክፍል ነው።
3. የፀሐይ ብርሃንና አየር ለዕፅዋት እድገት ያስፈልጋል።

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጣችሁ አማራጭ መልሶች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።**

1. ለዕጽዋት እድገት የሚያስፈልገው የቱ ነው?
   ሀ. አፈር ለ. ውሃ ሐ. አየር መ. ሁሉም
2. የስር ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ምግብ ማዘጋጀት
   ለ. ምግብ ማከማቸት
   ሐ. ዕጽዋቱን ከመሬት ጋር አጣብቆ መያዝ
   መ. ውሃና ማዕድናትን ወደ ግንድ ማስተላለፍ
3. ከመሬት በታች የሚገኝ የዕጽዋት አካል ክፍል የቱ ነው?
   ሀ. ስር ለ. ግንድ ሐ. ቅጠል መ. አበባ

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



**ሐ. በ"ሀ" ረድፍ ለሚገኙት ቃላት በ"ለ" ረድፍ ከተሰጡት መልሶች መካከል ትክክለኛ የመልስ ሆሄ በመምረጥ አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ምግብ የሚያዘጋጅበት | ሀ. ስር |
| 2. ውሃን ወደ ቅርንጫፉ ያስተላልፋል | ለ. ቅጠል |
| 3. የመራቢያ ክፍል | ሐ. ግንድ |
| 4. ከመሬት ጋር አጣብቆ ለመያዝ | መ. አበባ |

**መ. የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በተስማሚው ቃላት አሟሉ።**

1.____________ውሃና ማዕድናትን ወደ ግንድ ያስተላልፋል።

2. ዕፅዋት ____________የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው።

3.________ከመሬት በታች የሚገኝ የዕፅዋት አካል ክፍል ነው።

**ሠ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ ።**

1.ለዕፅዋት እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዘርዝሩ።

2.ከመሬት በላይ የሚገኙ የዕፅዋት አካል ክፍሎችን ዘርዝሩ።

3.ዕፅዋት ለሰው ልጅ ያለውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ።

# 3.3. በወረዳችን የሚገኙ እንስሳት

## ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡

- እንስሳትን (አጥቢዎች፣ ወፎች፣ አሳዎች፣ ገበሎ አስተኔዎችና እንቁራሪት አስተኔዎች) በውጫዊ ገጽታቸው በመዘርዘር ትመድባላችሁ፡፡
- ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ምግብ የጉልበት ምንጭ መሆኑን ትገልፃላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ☞ ብርቅዬ እንስሳት
- ☞ ገበሎ አስተኔዎች
- ☞ እንቁራሪት አስተኔዎች

## ሀ. በወረዳችን የሚገኙ እንስሳት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

1. በወረዳችሁ የሚገኙ ነባር እንስሳትን ዘርዝሩ፡፡
2. በወረዳችሁ የሚገኙ እንስሳትን በውጫዊ ገጽታቸው በመዘርዘር መድቡ፡፡

እንስሳት ህይወት ያላቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው፡፡ እንስሳት ይመገባሉ፣ ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ፣ ይራባሉ፣ ያድጋሉና እንዲሁም ይሞታሉ፡፡ በወረዳችን የተለያዩ እንስሳት ይኖራሉ፡፡

ለምሳሌ፡- በግ፣ ፍየል፣ በሬ፣ አህያ፣ ውሻ፣ ድመትና የተለያዩ ወፎች በወረዳችን በስፋት ከሚገኙት እንስሳት እንዲሁም ይመደባሉ::

ብርቅዬ እንስሳት ማለት በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ በአናሳ ቁጥር የሚኖሩ የእንስሳት ዝርያዎች ናቸው:: በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች ብዙ ብርቅዬ እንስሳት ይኖራሉ::

ለምሳሌ፡- ዋልያ፣ ቀይ ቀበሮ፣ ጭላዳ ዝንጀሮና የመሳሰሉት ናቸው::

## ለ. እንስሳትን በውጫዊ ገፅታቸው መመደብ

እንስሳት በአመጋገባቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው ሁኔታ፣ በአኗኗራቸው፣ በመራቢያቸው፣ በውጫዊ የሰውነት ገጽታቸውና ሽፋናቸው ይለያያሉ:: መመደብ ማለት የነገሮችን አንድነትና ልዩነት መሰረት በማድረግ የሚመሳሰሉትን በአንድ ላይ የማድረግ ዘዴ ነው::

**የቡድን ውይይት 6**

በቡድን በመሆን እንስሳትን በውጫዊ ገፅታቸው መመደብ

1. በወረዳችሁ የሚገኙ እንስሳትን ውጫዊ ገፅታቸውን በመዘርዘር መድቡ::
2. በወረዳችሁ ቆዳቸው በላባ፣ በፀጉርና በቅርፊት የተሸፈነ እንስሳትን ስም ተናገሩ::

እንስሳት በቆዳቸው ሽፋን መሰረት በሶስት ይመደባሉ:: እነርሱም፡- ቆዳቸው በላባ፣ በፀጉርና በቅርፊት የተሸፈነ ተብለው ይጠራሉ::




ምስል 3.15 ሰውነታቸው በላባ የተሸፈነ እንስሳት



ሥዕል 3.16 ሰውነታቸው በቅርፊት የተሸፈነ እንስሳት

**አጥቢዎች፡-** መሰላቸውን በመውለድ የሚራቡ፣ አብዛኛዎቹ ሰውነታቸው በፀጉር የተሸፈነ ነው፣ አብዛኛዎቹ ትላልቅ መጠን አላቸው። ምሳሌ፡- ዝሆን፣ ዋሊያ፣ ሰው፣ አይጥ፣ ድመትና የመሳሰሉት አጥቢዎች ውስጥ የሚመደቡ ናቸው።



ሥዕል 3.17 አጥቢዎች

**ወፎች፡-** ሰውነታቸው በላባ የተሸፈነ ነው፤ እንቁላል በመጣል ይራባሉ፤ መብረር የሚያስችላቸው ክንፍ አላቸው፡፡

ምሳሌ፡- ወፎች፣ እርግቦችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡




ምስል 3.18 ወፎች

**አሳዎች፡-** በውሃ ውስጥ ይኖራሉ፤ ሰውነታቸው በቅርፊት የተሸፈነ ነው። ምሳሌ፡- አሳዎች




ምስል 3.19 አሳዎች

**ገበሎ አስተኔዎች፡-** ሰውነታቸው በቅርፊት የተሸፈነ ነው ፤ በመሬትና በውሃ ውስጥ ይኖራሉ። ምሳሌ፡- አዞና እባብ



ምስል 3.20 እባብ እና አዞ

**እንቁራሪት አስተኔዎች ፡-** በመሬትና በውሃ ውስጥ መኖር ይችላሉ፤ ለስላሳና እርጥበታማ ቆዳ አላቸው፡፡
ምሳሌ፡- እንቁራሪቶች




ስዕል 3.21 እንቁራሪት አስተኔዎች

## ሐ. ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች

ለእንስሳት ለመኖር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡

ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች አየር፣ ውሃ፣ ምግብና መኖሪያ (መጠለያ) ናቸው፡፡



ስዕል 3.22 ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# ምግብ እንደ ጉልበት ምንጭ

ምግብ የጉልበት ምንጭ ነው፡፡ ምግብ ለሰውነታችን ሀይልና ሙቀት (ጉልበት) ሰጪ ነው፡፡

ጉልበት ማለት ስራን ለመስራት የሚያስችለን አቅም ማለት ነዉ፡፡ ምግብን በበቂ መጠንና በየዓይነቱ የምንመገብ ከሆነ ስራችንን በትክክል ለመስራት ያስችለናል፡፡

ለምሳሌ፡- ለመጫወት፣ ለማንበብ፣ ለመሮጥ፣ ለመተንፈስ፣ ለመናገርና ለመሳሰሉት ክንውኖች ጉልበት ያስፈልገናል፡፡

# ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ የምግብ ምድቦች

ጤናማ ምግብ ለሰውነታችን ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በተመጣጠነ መልኩ የያዙ የምግብ ምድብ ነው፡፡ ከባእድ ነገር ጋር ያልተቀላቀሉ፣ የንፅህና ጉድለት የሌለባቸው፣ ብዙ ጊዜ ያልቆየ፣ ዝቅተኛ የስኳር፣ የጨውና የቅባት መጠን የያዘ ምግብ ጤናማ ምግብ ይባላል፡፡

በተቃራኒው የተበላሹና የንፅህና ጉድለት የሚታይባቸው፣ ከፍተኛ የስኳር፣ የጨውና የቅባት መጠን የያዙ እንዲሁም ከባዕድ ነገሮች ጋር የተቀላቀሉ ምግቦች ደግሞ ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች ይባላሉ፡፡

## የቡድን ውይይት 7

ዓላማ፡- ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ የምግብ ምድቦችን መለየት

1. ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችን ግለፁ፡፡
2. ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችን ዘርዝሩ፡፡



ምስል 3.23 ጤናማ የምግብ ምድቦች




ሥዕል 3.24 ጤናማ ያልሆኑ የምግብ ምድቦች



ምስል 3.25 የተበላሹ ምግቦች

## መልመጃ 3.3

**ሀ. የሚከተለት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት " ትክክል ካልሆኑ "ሀሰት " በማለት መልሱ።**

1. እንስሳትን በውጫዊ ገፅታቸው መሰረት መመደብ ይቻላል።
2. አየር ለእንስሳት መኖር አስፈላጊ ነው።
3. ወፎች ሰውነታቸው በላባ ተሸፈነ አይደለም።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጣችሁ አማራጭ መልሶች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።**

1.ከሚከተሉት ውስጥ ስለ እንስሳት ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. መራባት ለ. መንቀሳቀስ

ሐ. ምግብ ማዘጋጀት መ. መመገብ

2. ሰውነታቸው በፀጉር የተሸፈነና መሰላቸውን በመውለድ የሚራቡ እንስሳት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. አሳዎች ለ. ወፎች

ሐ. አጥቢዎች መ. እንቁራሪቶች

3. ከሚከተሉት ውስጥ በመሬት ላይና በውሃ ውስጥ መኖር የሚችሉት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ገበሎ አስተኔዎች ለ. እንቁራሪት አስተኔዎች

ሐ. አሳዎች መ. ሀ እና ለ

### ሐ. ለሚከተለት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ ።

1. በወረዳችሁ የሚገኙ እንስሳት ከዘረዘራችሁ በኋላ ቆዳቸው በላባ፣ በፀጉርና በቅርፊት የተሸፈነ በማለት መድቡ።
2. እንስሳት ለመኖር የሚያስፈልጉቸው ነገሮችን ዘርዝሩ።
3. በወረዳችሁ የሚገኙ አጥቢ እንስሳትን ስም ፃፉ።

## 3.4. በወረዳችን የሚገኙ ቁሳዊ ሀብቶች

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ ፡-

- መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉና በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሶችን ትለያላችሁ።
- ከወዳደቁ ነገሮች ሊሠሩ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮችን ትገምታላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- ☞ ቁሳዊ ሀብት
- ☞ መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ
- ☞ በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ

## ቁሳዊ ሀብት

በወረዳችን ብዙ አይነት መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉና በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶች ይገኛሉ። ቁሳዊ ሀብቶች የምንላቸው ድንጋይ፣ አፈር፣ ውሃ፣ አየር፣

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



ወረቀት፣ቁርጥራጭ ብረት፣ ካርቶን፣ መስታወት፣ መኪና፣ ጎማና ፕላስቲክ ናቸው።

## ሀ. መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶች

ለምሳሌ፡- ሀይላንድ፣ ወረቀት፣ ፕላስቲክስ፣ ቁርጥራጭ ብረት፣ ካርቶን፣ የመሳሰሉት ይገኛሉ። እነዚህን ቁሳዊ ሀብቶች መልሰን የተለያዩ ጠቃሚ የሆኑና ተመሳሳይ ነገሮችን በመስራት መጠቀም ይቻላል።





ምስል 3.26 መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶች

### የቡድን ውይይት 8

ቀጥሎ በቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. በወረዳችሁ የሚገኙ መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉና በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶችን ዘርዝሩ።

2. ከወዳደቁ ነገሮች ሊሠሩ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮችን ዘርዝሩ።

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## ለ. በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶች፡-

የምንላቸው እንደገና መልሰን ለሌላ ጥቅም የምንጠቀምባቸው ሲሆኑ ለምሳሌ፡- ጠርሙስ፣ ሀይላንድ፣ ጀሪካንና ሌሎች እቃዎች በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶች ናቸው፡፡

## ሐ. ከወዳደቁ ነገሮች ሊሠሩ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች፡-

ብስባሽ (ኮምፖስት) ከወዳደቁ ቅጠሎችና ከተረፉ ምግቦች ማዘጋጀትና መጠቀም ይቻላል፡፡ አዲስና ተመሳሳይ ወረቀቶችና ካርቶኖች ከወዳደቁ ወረቀቶችና ካርቶኖች ማዘጋጀት ይቻላል፡፡



ምስል 3.27 ከወዳደቁ ነገሮች ሊሠሩ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች

## ተግባራዊ ክንውን 2

1. በወላጆቻችሁ እገዛ በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ነገሮች (ቁሶች) መልሰውና በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ለዩ::
2. ከሚከተሉት ውስጥ ሁለቱን መርጣችሁ ከሰራችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አሳዩ::

ሀ. ሳይክል ለ. ራዲዮ ሐ. ብርጭቆ መ. ሰዓት

## መልመጃ 3.4

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት " ትክክል ካልሆኑ "ሀሰት " በማለት መልሱ::**

1. በአካባቢያችን ብዙ የተለያዩ መልሰውና በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶች ይገኛሉ::
2. በአካባቢያችን የሚገኙ ቁሳዊ ሀብቶችን በመጠቀም ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን መስራት ይቻላል::
3. የተለያዩ ጠርሙሶችን በድግግሞሽ መጠቀም አይቻልም::

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጣችሁ አማራጭ መልሶች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::**

1. በወረዳችን በቀላሉ የሚገኘው ቁሳዊ ሀብት የቱ ነው?

ሀ. ወረቀት ለ. ሀይላንድ ሐ. ብረታብረት መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉት ውስጥ ከወዳደቁ ቁሳዊ ሀብቶች ሊሰራ የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. ፕላስቲክ ለ. ኮምፖስት ሐ. ወረቀት መ. ሁሉም

### ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ ።

1. በወረዳችሁ የሚገኙና መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ሀብቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. በድግግሞሽ መልሰው ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡
3. በወረዳችሁ የሚገኙ ቁሳዊ ሀብቶችን በመጠቀም ሊሰሩ የሚችሉ ነገሮች ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## 3.5. የወረዳችንን አካባቢ መንከባከብ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- በወረዳችን የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የፓርክን ምንነት ትገልጻላችሁ፡፡
- በወረዳችሁ የሚገኘውን ፓርክ ጠቀሜታ ትለያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ፓርክ
- አካባቢ
- መንከባከብ

### ሀ. በወረዳችንን የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ

የተፈጥሮ ሀብት ማለት በአከባቢያችን በተፈጥሮ የሚገኝ ለሰው ልጅ ጥቅም የሚሰጥ ማንኛውም ነገር ነው፡፡ የወረዳችንን አካባቢ መንከባከብ ማለት በወረዳችን የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብትን ለብክነትና ለጉዳት ከሚዳርጉ ሁኔታዎች መከላከል፣ መጠበቅና መንከባከብ ማለት ነው፡፡ ለአካባቢያችንን ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ

ካላደረግን የተፈጥሮ ሀብቶቻችን ሊጎዱና ሊጠፉ ይችላሉ። ነገር ግን በጥንቃቄና በንክብካቤ ከተጥቀምንባቸው ዘላቂ አገልግሎት ይሰጡናል። የተፈጥሮ ሀብት የምንላቸው አየር፣ ውሃ፣ አፈር፣ ዕፅዋትና እንስሳት ናቸው። የአካባቢያችን የተፈጥሮ ሀብቶች በተለያዩ ምክንያቶች ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው ስለሆነ ልንጠብቃቸውና ልንከባከባቸው ይገባል። ስለዚህ አካባቢያችንን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መንከባከብ አለብን።





ሥዕል 3.28 የአካባቢ እንክብካቤ

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



የአካባቢ እንክብካቤ ዋና ዋና መንገዶች ዕፅዋትን መትከልና መንከባከብ፤ ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ፤ የደን ቃጠሎን መከላከል፤ ፅዳት ዘመቻ ላይ መሳተፍና ስለ አካባቢ እንክብካቤ ለሰዎች ግንዛቤ መፍጠር ናቸው።

## ለ. በወረዳችን የሚገኙ ፓርኮችና ጠቀሜታቸው

የተለያዩ እንስሳትን እና እጽዋትን ጠብቅ ለማቆየት የሚያስችል ጥብቆ ቦታ ፓርክ ይባላል። ፓርክ ለአንድ አካባቢ የተለያየ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል። ከእነዚህም መካከል ለመዝናኛነት፣ ለትምህርታዊ ጉብኝት፣ ለገቢ ምንጭነት፣ ለእንስሳት መኖርያነት፣ እንስሳትን ለመንከባከቢያነት እና የመሳሰሉት ናቸው።




ሥዕል 3.29 የወዳጅነት ፓርክ

### የቡድን ውይይት 9

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ

1. በአካባቢያችሁ የሚገኘውን ፓርክ ለምን ይጠቅማል?
2. ፓርኩ ባይኖር ኖሮ ሰዎች የት ይዝናኑ ነበር?

## ሐ. የተፈጥሮ ሀብቶች ጠቀሜታ

የተፈጥሮ ሀብቶች ከሚሰጡት ጠቀሜታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፡- ለምግብ ምንጭነት፣ ለልብስ፣ ለመጠለያ፣ ለገቢ ምንጭነት፣ ለመጓጓዣ፣ ለመዝናኛ፣ ቱሪስት መስህብነት የተለያዩ የመገልገያ ቁሳቁሶችንና ጌጣጌጦችን ለመስራት ያገለግላሉ።

### የቡድን ሥራ 3

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ከሰራችሁ በኂላ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅረቡ።

1. ተፈጥሮ የሰውን ፍላጎት እንዲያሟላ ባለው ሚና ላይ ትኩረት በማድረግ በሰው እና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ዝምድና ግለፁ፣
2. የተፈጥሮ ሀብቶች የሚሰጧቸውን ጥቅሞች በፅሁፍ ዘርዝሩ።
3. የተፈጥሮ ሀብቶች ባይኖሩ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ለመምህራችሁ አስረዱ።

## መልመጃ 3.5

**ሀ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ “እውነት “ ትክክል ካልሆኑ ”ሀሰት “ በማለት መልሱ፡፡**

1. አየር፣ ውሃ፣ አፈር፣ ዕፅዋትና እንስሳት የተፈጥሮ ሀብት ምሳሌዎች ናቸው፡፡
2. ለአካባቢያችን ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ ማድረግ አያስፈልግም፡፡
3. ዕፅዋትን መትከልና ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ አካባቢን መንከባከብ ይባላል፡፡
4. የተፈጥሮ ሀብቶች የሰው ልጅን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት አይጠቅሙም፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጣችሁ አማራጭ መልሶች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. አየር ለ. ውሃ ሐ. አፈር መ. ሁሉም
2. የተፈጥሮ ሀብት ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ለምግብነት ለ. ለመጠለያነት
   ሐ. ለገቢ ምንጭነት መ. ሁሉም

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ ፡፡**

1. የተፈጥሮ ሀብት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የተፈጥሮ ሀበት ጠቀሜታን ግለፁ፡፡
3. በወረዳችሁ የሚገኙ ፓርኮች ጠቀሜታ አብራሩ፡፡

## የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ

- የአየር ሁኔታ ማለት በየዕለቱ በአንድ አካባቢ የሚኖር የዝናብ፣ የሙቀት፣ የንፋስ ሁኔታ የመሳሰሉት መገለጫ ነው::
- የአየር ንብረት ለረጅም ጊዜ በአንድ አካባቢ የታየ እለታዊ የአየር ለውጥ አማካይ ውጤት ስያሜ ነው::
- የአንድ አካባቢ አየር ንብረት በሰዎች አኗኗር ላይ፣ አመጋገብና የአለባበስ ባህል ላይ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን ያሳድራል::
- በአገራችን አራት ዋና ዋና ወቅቶች አሉ:: እነርሱም:- ፀደይ፣ ክረምት፣ በጋና በልግ ናቸው::
- የዕፅዋት አካል ክፍሎች በመጠናቸውና በቅርፃቸው እንዲሁም በተግባራቸው ይለያያሉ:: ግንድ፣ ቅጠል፣ ስርና አበባ ዋና ዋና የዕፅዋት ክፍሎች ናቸው::
- ለዕፅዋት እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮች አየር፣ አፈር፣ ውሃና የፀሐይ ብርሃን ናቸው::
- እንስሳትን በውጫዊ ገጽታቸው መሰረት አጥቢዎች፣ ወፎች፣ አሳዎች፣ ገበሎ አስተኔዎችና እንቁራሪት አስተኔዎች ተብለው ይመደባሉ::
- ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች አየር ፣ ውሃ፣ ምግብና መኖሪያ (መጠለያ) ናቸው::
- የተፈጥሮ ሀብት የምንላቸው አየር፣ ውሃ፣ አፈር፣ ዕፅዋትና እንስሳት ናቸው:: የአካባቢያችን የተፈጥሮ ሀብቶች በተለያዩ ምክንያቶች ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው ስለሆነ ልንጠብቃቸውና ልንከባከባቸው ይገባል::

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት " ትክክል ካልሆኑ "ሀሰት " በማለት መልሱ።**

1. የአየር ሁኔታ በዕየለቱ የሚለዋወጥ የአየር ባህርይ ነው።
2. የአየር ንብረት በአንድ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የተመዘገበ አማካኝ የአየር ሁኔታ ነው።
3. አየር፣ ውሃ፣ ምግብና መጠለያ ለእንስሳት አስፈላጊ ናቸው።
4. አበባና ስር የእጽዋት አካል ክፍል ውስጥ አይመደቡም።
5. ሰውነታችን ጉልበት የሚያገኘው ከምግብ ነው።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጣችሁ አማራጭ መልሶች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።**

1. ምግብ የሚዘጋጅበት የዕፅዋት አካል ክፍል የቱ ነው?

   ሀ.ቅጠል ለ. ስር ሐ. አበባ መ. ግንድ

2. የስር ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ.ምግብ ማከማቸት

   ለ. ውሃን ወደ ግንድ ማስተላለፍ

   ሐ. ምግብ ማዘጋጀት

   መ. ዕፅዋቱን ከአፈር ጋር አጣብቆ መያዝ

3. ከሚከተሉት ውስጥ ለዕፅዋት እድገት የሚያስፈልገው የቱ ነው?

   ሀ. አፈር ለ. ውሃ ሐ. አየር መ. ሁሉም

4. ከሚከተሉት ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልገው የቱ ነው?

ሀ. አየር     ለ. ውሃ     ሐ. ምግብ     መ. ሁሉም

**ሐ. በ”ሀ” ረድፍ የሚገኙትን ሀረጋት በ”ለ” ረድፍ ከተዘረዘሩት እንስሳት ጋር አዛምዱ፡፡**

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ሰውነታቸው በላባ የተሸፈነ | ሀ. አጥቢዎች |
| 2. ሰውነታቸው በቅርፊት የተሸፈነ | ለ. ወፎች |
| 3. መሰሎቻቸውን የሚወልዱ | ሐ. ገበሎ አስተኔዎች |

**መ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ ፡፡**

1. የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ምንነት አብራሩ፡፡
2. የዕፅዋት አካል ክፍልን በስዕል ሰርታችሁ አሳዩ፡፡
3. ለዕፅዋት እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡
4. ብርቅዬ እንስሳት ማለት ምን ማለት ነው? የብርቅዬ እንስሳት ምሳሌ ጥቀሱ፡፡

# ፍተሻ

ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለፅ የ "✓" ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ

1. የአየር ሁኔታን ምንነት እገልፃለሁ። ☐
2. የአየር ሁኔታን ምሳሌዎች እጠቅሳለሁ። ☐
3. የአየር ንብረት ምንነትን እገልፃለሁ። ☐
4. የአየር ንብረት በአኗኗር ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ እገልፃለሁ። ☐
5. ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ የምግብ ምድቦችን እለያለሁ። ☐
6. በአካባቢያችን በስፋት የሚገኙ ዕፅዋትን እለያለሁ። ☐
7. ለዕፅዋት ዕድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን እለያለሁ። ☐
8. የዕፅዋትን የተለያዩ ጥቅሞች እዘረዝራለሁ። ☐
9. ለእንስሳት መኖር የሚያስፈልጉ ነገሮችን እዘረዝራለሁ። ☐
10. ምግብ የጉልበት ምንጭ መሆኑን እገልፃለሁ። ☐
11. እንስሳትን (አጥቢዎች፣ ወፎች፣ አሳዎች፣ ገበሎ አስተኔዎችና እንቁራሪት አስተኔዎች) በውጫዊ ገጽታቸው በመዘርዘር እመድባለሁ። ☐
12. መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉና በድግግሞሽ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሶችን እለያለሁ። ☐
13. ከወዳደቁ ነገሮች ሊሠሩ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮችን እገምታለሁ። ☐

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# ምዕራፍ አራት

# ማኅበራዊ አካባቢ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የግል ንጽሕና (እጅ መታጠብና ጥርስን ማጽዳት) መጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ፡፡
- የቤተሰብ አባላትና ፍላጎታቸውን ትገልጻላችሁ፡፡
- የቤተሰብ ጤና መጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ
- በትምህርት ቤትና በአካባቢው የሚገኙ የማኅበረሰብ አባላትን ትለያላችሁ.፡፡
- የአቻ ግንኙነትን በማዳበር በትምህርት ቤት የተለያዩ ተግባራትን ታከናዉናላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤት ደንቦችንና መመሪያዎችን ታከብራላችሁ፡፡

## የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

4.1. የቤተሰብ አባላትና ፍላጎታቸው

4.2. በትምህርት ቤት ተግባራትን በጋራ ማከናወንና የአቻ ግንኙነትን ማዳበር

4.3. ንጽሕናና የግል ጤና

# 4.1.የቤተሰብ አባላትና ፍላጎታቸው

## ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፤

- የግል ንጽሕና (እጅ መታጠብና ጥርስን ማጽዳት) መጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ::
- የቤተሰብ አባላትና ፍላጎታቸውን ታብራራላችሁ::
- የቤተሰብ ጤና መጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ ታብራራላችሁ::

**ቁልፍ ቃላት**

- ማኅበራዊ አካባቢ
- የቤተሰብ ጤና
- የግል ንጽህና
- ጤና አጠባበቅ

# ማኅበራዊ አካባቢ

## ተማሪዎች ማኅበራዊ አካባቢ ምንድን ነዉ?



ሥዕል 4.1. ማኅበራዊ ግንኙነት - ልጆች በጋራ ሲያጠኑ

### የቡድን ውይይት 1

ዓላማ፤ ስለማኅበራዊ አካባቢ ምንነት መረዳት

መመሪያ፤ተማሪዎች ስለማበራዊ አካባቢ ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

- ማኀበራዊ አካባቢ ማለት ምን ማለት ነው?

ማኀበራዊ አካባቢ ማለት በሰው ልጅ ዕውቀት፤ ችሎታና መሣሪያ የተደራጀ ወይም የተሠራ ተቋም (ነገር) ማለት ነው፡፡



ሥዕል 4.2. ማኅበራዊ አካባቢ-ልጆች በቤተ መጻሕፍት ሲያጠኑ

## የቡድን ውይይት 2

ዓላማ:- ስለ ማኅበራዊ አካባቢ ምንነት መረዳት

መመሪያ:-ተማሪዎች በሥዕል 4.2 መሠረት ስለ ማኅበራዊ አካባቢ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን ለክፍል መምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

ከየወረዳችሁ ዋና ዋና ማኅበራዊ አካባቢ አራቱን ጻፉ፡፡

በአዲስ አበባ በአንዱ ወረዳ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ማኅበራዊ አካባቢዎች እንደ ጤና ጣቢያ፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ ባንክ ቤት፣ ሸማቾች ሱቅ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እናንተም በወረዳችሁ ያሉትን መጥቀስ ትችላላችሁ፡፡




ሥዕል 4.3 ማኅበራዊ አካባቢ-ተማሪዎች በቡድን ሲወያዩ

## የቡድን ውይይት 3

**ዓላማ:- ስለ ማኅበራዊ አካባቢ ምንነት መረዳት**

**መመሪያ:- ተማሪዎች ስለማበራዊ አካባቢ ከተወያያችሁ በኋላ ከታች ለቀረበው ጥያቄው መልሳችሁን ለክፍል መምህራችሁ አቅርቡ፡፡**

**ማኅበራዊ አካባቢን በምሳሌ አስረዱ፡፡**

አዲስ አበባ ቤተ መንግሥት የሚገኘውን የአንድነት ፓርክ እንደ አንድ ማኅበራዊ አካባቢ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ፓርኩ በውስጡ የታሪክ፣ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሥራዎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡

ማኅበራዊና አካባቢ:- በሰው ልጅ ዕውቀት፣ ክሂል (ችሎታ)፣ መሣሪያዎችና ተቋም የተደራጁ ወይም የተሠሩ ነገሮችን ያንፀባርቃል፡፡ ሕንፃዎች፣ መንደሮች፣ ከተሞች፣ ፋብሪካዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች በማኅበራዊ አካባቢ የሚካተቱ ተቋማት ናቸው፡፡




ሥዕል 4.4. ማኅበራዊ አካባቢ

## ሀ. የቤተሰብ ጤና- የንጽሕና ጠቀሜታ፤ እንቅስቃሴና ዕረፍት



ሥዕል 4.5. የቤተሰብ የእረፍት ጊዜ

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## የቡድን ውይይት 4

በጥንድ ወይም በቡድን ስለቤተሰብ ጤና መገንዘብ

ዓላማ:- የንጽህና ጠቀሜታ፣ የእንቅስቃሴና የዕረፍት አስፈላጊነት መግለጽ

መመሪያ:- በሥዕል.4.6 መሠረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ እና በቡድን ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ። ስዕሉ 4.6 በቦታወ ላይ ይቀመጥ

የመወያያ ነጥቦች:-

1. እጅ መታጠብና ጥርስ ማጽዳት ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
2. እንቅስቃሴና እረፍት ማድረግ ለምን ያስፈልጋል?
3. በእያንዳንዱ ምሽት ምን ያህል ሰዓት መተኛት አለብን? ለምን?

ዘወትር እጅን በሣሙናና በውኃ ሲታጠቡ በሽታ አምጪ ነገሮችን እናስወግዳለን፤ እጅም ንጹሕ ይሆናል። ጥርስም እንዲሁ በጥርስ ሣሙና (ኮልጌት) ማጽዳት የጥርስ ንጽሕና እንዲጠበቅ ይረዳል።

አንድ ቤተሰብ በየጊዜው አካላዊ እንቅስቃሴ (ስፖርት) በመሥራት ጤናው እንዲጠበቅ ማድረግ ይችላል። ከዚህም ሌላ አንድ ሰው በቀን ለስምንት ሰዓታት በመተኛት አካሉንና ሰውነቱን ከድካም ያሳርፋል፤ ጤናውም የተጠበቀ ይሆናል።

## የቡድን ውይይት 5

**በጥንድ ወይም በቡድን ስለ ቤተሰብ ጤና መገንዘብ**

**ዓላማ:-** የንጽህና ጠቀሜታ፣ የእንቅስቃሴና የዕረፍት አስፈላጊነት መግለጽ


**መመሪያ:-** በሥዕል.4.6 መሠረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ እና በቡድን ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

**የመወያያ ነጥቦች፤**

1. ሰውነታችንን በመደበኛነት ለምን እንታጠባለን?
2. መታጠብ ያለብን የት ነው? ለምን?
3. መታጠብ የሌለብንስ የት ነው? ለምን? ሐሳባችሁን ጻፉ።
4. ንጹሕ ልብስን መልበስ የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድን ነዉ?
5. ንጹሕ ልብስ መልበስ ስለሚኖረው ጠቀሜታ ግጥም ጻፉ።

ሰውነታችንን በመደበኘነት የምንታጠበው ሰውነታችንን ከበሽታ አምጪ ነገሮች ለመከላከልና ጤናችንን ለመጠበቅ ነው። ሰውነታችንን መታጠብ ያለብን ደግሞ በተገቢው የገላ መታጠቢያ ቦታ (ሻወር ቤት) ሊሆን ይገባል፤ ምክንያቱም ከሰውነት የሚወጣ ቆሻሻ አካባቢያችንን እንዳይበክል ለመጠበቅ ስለሚረዳ ነው። በወንዝ፣ ሜዳ ላይ ወይም አካባቢን በሚበክል ቦታ መታጠብ የለበትም።

ንጹሕ ልብስ መልበስ ያስደስታል፤ ከበሽታ አምጪ ነገሮች




ሥዕል 4.6. የቤተሰብ ንጽሕና አጠባበቅ

እንደ ተባይ ካሉ የፀዳ ስለሆነ ነው፡፡ስለዚህ ጤናችን ይጠበቃል፡፡

## ንጹሕ ልብስ (ግጥም)

ያለንን ልበስ አጥበን፤

ሁሌ ንጹሕ ለብሰን፤

ደስተኛ እንኖናለን፤

ጤናችን ተጠብቀን፡፡

ጤነኛ ቤተሰብ ማለት አለመታመም፤ ደኅና መሆንና ደስተኛ መሆን ማለት ነው፡፡ አንድ ቤተሰብ በአካሉና በአእምሮ ላይ ምንም ሕመም ከሌለው ጤነኛ ቤተሰብ ይባላል፡፡ ጤነኛ ቤተሰብ ደስተኛና በራሱ ጥሩ ስሜት የሚሰማው ነው፡፡

በየጊዜው ሰዉነታችንን፤ ፀጉራችን ስንታጠብና የምንለብሳቸውን ልብሶች ስናጥብ የግል ንጽሕና ጠበቅን ማለት ነው፡፡ የግል ንጽሕናን በመጠበቅ ራሳችንን ከሽታ ለመከላከል፣ ንቁና ደስተኛ ለመሆን፣ ሥራችንን በትጋት ለማከናወን ይጠቅማል፡፡

ከዚህ በተቃራኒ የግል ንጽሕናን አለመጠበቅ ደግሞ ለተለያዩ በሽታዎች ለምሳሌ እንደ እከክ፤ የዓይን ሕመም (ትራኮማ)፤ ፎረፎር፤ ወስፋት፤ ኮሌራ (አተት)፤ ተስቦና ለመሳሰሉት በሽታዎች ያጋልጣል፡፡

ስለሆነም የቤተሰብ ጤና የሚጠበቀው እጅ በመታጠብ፣ ጥርስን በማጽዳት፣ ሰውነትን በመደበኛነት በመታጠብ፣ ንጹሕ ልብስ በመልበስ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግና እንዲሁም በቀን ስምንት ሰዓት በመተኛትና በቂ እረፍት በማድረግ ጭምር ነው፡፡

## ለ.የቤተሰብ አባላትና ፍላጎታቸዉ

ተማሪዎች ! አንደኛ ክፍል እያላችሁ ስለ ቤተሰብ አባላትና መሠረታዊ ፍላጎት ተምራችኋል። አሁን ደግሞ ስለቤተሰብ አባላት ሌሎች ፍላጎቶች ትማራላችሁ።

የቤተሰብ አባላት ሌሎች ፍላጎቶች ምን ምንድን ናቸው?





ሥዕል 4.7. የቤተሰብ አባላት ሌሎች ፍላጎቶች

(ተማሪዎች! ሥዕሉ ምንን ያመለክታል?)

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



የአንድ ቤተሰብ አባላት ከመሠረታዊ ፍላጎቶች ሌላ የተለያዩ ፍላጎቶች አሉዋቸው። ለምሣሌ:- መኪና፣ ሽርሽር፣ ጉብኝት፣ ዋና፣ ስፖርታዊ ጨዋታ፣ በሙዚቃ ዝግጅት ተሳተፊ የመሆን ፍላጎት ሊሆኑ ይችላል። ስለዚህ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባላት ከመሠረታዊ ፍላጎቶች ውጭ ሌሎች የተለያዩ ፍላጎቶች ይኖሩታል።

## የግል ሥራ 1

ዓላማ:- የቤተሰብ አባሎቻችሁን የግል ፍላጎት መግለጽ

መመሪያ:-

ተማሪዎች በሥዕል 4.7 መሠረት ከቤተሰብ ጋር ተወያይታችሁ የቤተሰብ አባላችሁን አንድ አንድ ፍላጎት በጽሑፍ አቅርቡ።

1. የቤተሰብ አባሎቻችሁ ስንት ናቸው?
2. የእያንዳንዳችሁን ቤተሰብ አባል አንድ አንድ ፍላጎት ጠይቁና በጽሑፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

ተማሪዎች! የቤተሰባችሁ ብዛት ስንት እንደ ሆነ ትጽፋላችሁ። ከዚያም ከእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እናት፣ አባት፣ እህት፣ ወንድምና የሌሎች አባላትን ፍላጎታቸውን በጽሑፍ አቅርቡ። ለምሣሌ:- አባት መኪና የመግዛት ፍላጎት ይኖረዋል፤ እናት ደግሞ በማሽን ሹራብ የመሥራት ፍላጎት ሊኖራት ይችላል እና ሌሎችን በዚህ ዓይነት ምሣሌ መጻፍ ይቻላል ማለት ነው።

## ሐ. በትምህርት ቤት ያሉ ሰዎችና በዙሪያው ያሉ የአካባቢው ማኅበረሰብ ፍላጎታቸውን እንዴት እንደሚያገኙ መለየት

ተማሪዎች! ፍላጎት ማለት ምን ነው?

አንደኛ ክፍል በትምህርት ቤታችሁ ስለሚገኙ ነገሮች ተምራችኋል:: አሁን ደግሞ በትምህርት ቤት ያሉ ሰዎችና በዙሪያው ያሉ የአካባቢው ማኀበረሰብ ፍላጎታቸውን እንዴት እንደሚያገኙ ትለያላችሁ::

ፍላጎት ማለት አንድ ነገርን ለማግኘት ማሰብና መሞከር ነው:: በትምህርት ቤት ውስጥ የትምህርት ቤት ማኀበረሰብ አባላት ይገኛሉ:: የትምህርት ቤት ማኀበረሰብ አባላት የሚባሉት ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች ናቸው::

በትምህርት ቤት ዙሪያም የተለያዩ ማኀበረሰቦች ይገኛሉ:: የአካባቢ ማኀበረሰብ፣ የወረዳው ማኀበረሰብ ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ:: በትምህርት ቤት ዙሪያ ያሉ የአካባቢ ማኀበረሰቦች ፍላጎታቸውን በተለያየ መንገድ ያገኛሉ:: ለምሣሌ:- የታክሲ፣ የትምህርት፣ የፋርማሲ፣ የስልክ፣ የሱቅ እና የመሳሰሉት አገልግሎት ይሰጣል:: ስለሆነም የአካባቢው ማኀበረሰብ ፍላጎቱን በእነዚህና በሌሎች መንገዶች ያሟላሉ::

በትምህርት ቤትም ተማሪዎች በልዩ ልዩ ክበባት፣ በቤተ መጻሕፍት፣ በፈጠራ ሥራዎች፣ በሚኒ ሚዲያ፣ ለዓባይ ቦንድ በማዋጣት፣ ጨዋታዎች በመጫወት የመሣሰሉት ላይ በመሳተፍ ፍላጎታቸውን ያሟላሉ::

| የትምህርት ቤት ፍላጎት | የአካባቢ ማኅበረሰብ ፍላጎት |
|---|---|


















ሥዕል 4.8 የማኅበረሰብ ፍላጎት

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## የቡድን ውይይት 6

ዓላማ:- ሰዎች በአካባቢያቸው ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚያስችላቸው ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ገጽታዎችን የሚሰጡ አገልግሎቶችን መግለጽ::

መመሪያ:- ቡድን በመመሥረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ ግለጹ::

የመወያያ ጥያቄዎች:-

- ቤተሰቦቻችሁ ምግብ ለመግዛት የሚሄዱት የት ነው?
- በአካባቢው አርሶ አደሮች ለገበያ የሚያቀርቡበት ማከማቻ መጋዘን ወይንም የገበያ ቦታ ባይኖር ምን ይከሰት ነበር?
- በአካባቢው የሚገኘውን ፓርክ እነማን ይጠቀሙበታል? ለምን ይጠቀሙበታል? ፓርክ ባይኖር ኖሮ እነዚህ ተግባራት የሚከናወኑበት አማራጭ ይኖር ነበር? ወይንስ የት ቦታ ማድረግ ይቻል ነበር?

ተማሪዎች! ቤተሰቦቻችሁ ምግብ ለመግዛት በአካባቢያችሁ ወደአለው የምግብ መሸጫ ሱቆች፤ ሱፐርማርኬቶችና የገበያ አዳራሾች በመሄድ የምግብ ሸቀጦች ሊገዙ ይችላሉ::

በአካባቢያችሁ አርሶ አደሮች ለገበያ የሚያቀርቡት ማከማቻ መጋዘን ባይኖር ኖሮ ለምሣሌ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ምስር፣ አተር፣ ባቄላና የመሣሠሉት የምርት እጥረት ይከሰት ነበር::

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



ፓርክ ሰዎች ለመዝናናት፣ ለመጎብኘት፣ መንፈስን ለማደስና ትምህርት ለማግኘት የሚሄዱበት ቦታ ነው። ስለዚህ በአካባቢያችሁ ፓርኮች ካሉ የዚህ ተጠቃሚ እናንተና ማንኛውም ሰው ሊሆን ይችላል። ፓርኮች ከሌሉ ደግሞ ሌሎች አማራጮችን እንደ መናፈሻ ቦታዎች፣ መዋኛ ቦታዎች፣ መጫወቻ ቦታዎችና እንዲሁም ከአካባቢያችሁ ወጣ ብላችሁ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በመሆን በመኪና ሆነ በእግር ጉዞ በማድረግ ሌሎች ቦታዎችን ማየትና መጎብኘት ይቻላል።

## የቡድን ውይይት 7

ዓላማ:- ሰዎች በአካባቢያቸው ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚያስችላቸው ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ገጽታዎችን መግለጽ።

መመሪያ:- ቡድን በመመሥረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሐሳብ ለመምህራችሁ በጽሑፍ ግለጹ።

የመወያያ ጥያቄዎች:-

1. የመጫወቻ ቦታው ቢበላሽ ምን ይሰማችኋል?
2. ማኅበረሰባቸው የተወሰኑ አገልግሎቶቹን እና አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተያያዙ ሙያዎችን (ለምሳሌ፤ የጽዳት ሠራተኛ፤ የውሃና ፍሳሽ ሠራተኛ፤ መረጃና ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ሠራተኛ) በመለየት የሰዎችን ፍላጎት እንዴት እንደሚያሟሉ ግለጹ።
3. የናንተንና የሌሎች ሰዎችን ፍላጎት እንዴት እንደሚያሟላ ግለጹ።

በትምህርት ቤት የመጫወቻ ቦታዎች ለምሣሌ የጂምናስቲክ መሥሪያ፣ የሸርተቴ መጫወቻ፣ የዥዋዢዌ መጫወቻ፣ የሽክርክሪት መጫወቻ፣ የመሣሠሉትን የጨዋታ ፍላጎታችሁን ያሟላሉ፡፡ነገር ግን በተለያየ ምክንያት ቢበላሹ የጨዋታ ፍላጎታችንን ማሟላት አይቻልም፡፡


ለአካባቢ ማኅበረሰብ የተወሰኑ አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተያያዙ ሞያዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የተወሰኑትን እንደምሣሌ ትመለከታላችሁ፤

- **የጽዳት ሠራተኛ:-** ባለሙያ ለአካባቢው ማኅበረሰብ የጽዳት አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- **የውኃና ፍሳሽ ሠራተኛ:-** ንጹሕ የመጠጥ ውኃ አገልግሎትና የመጸዳጃ ቤት ፈሣሽ ማስወገድ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- **የመረጃና ቴክኖሎጂ አገልግሎ ሠራተኛ**:- የኢንተርኔት፣ የስልክ፣ የኮምፒዩተር፣ የአይ.ሲ.ቲ፣ የሜትሪዮሎጂ፣ የወታደራዊ መረጃ የመሣሠሉትን አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- **የማኅበረሰብ ፖሊስ ሠራተኛ**:- የአካባቢን ማኅበረሰብ ደኅንነት መጠበቅ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- **የፋርማሲ ሠራተኛ**:- በሐኪም የታዘዘ መድሐኒት የመሸጥ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- **የዳቦ ጋጋሪ ሠራተኛ**:- ዳቦ ለአካባቢ ማኅበረሰብ ለገበያ የማቅረብ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ተማሪዎች የናንተንና የሌሎችን ፍላጎት እንዴት እንደ ሚያሟላ አሁን በቀላሉ ተረድታችኋል፡፡

## መ. የመረጃና ቴክኖሎጂ ግብኣት የት ሊገኝ ይችላል ?

ተመሪዎች! መረጃና ቴክኖሎጂ ምንድን ነው? መልሱን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



ሥዕል.4.9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ማሣሪያዎች

መረጃና ቴክኖሎጂ እንደ ኮምፒዩተር፣ ስልክ፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ማቀዝቀዣ የመሳሰሉትን መሣሪያዎች በመጠቀም መረጃን ማስቀመጥ፣ መጠቀምና መላክ የሚቻልበት ዘዴ ነው፡፡ መረጃና ቴክኖሎጂ ሰዎች በግል፣ በጋራና በቡድን ሥራቸውን በተቀላጠፈ መንገድ እንዲሠሩ፣ እንዲላላኩና እንዲገናኙ ያግዛል፡፡ ስለዚህም ሰዎች ኮምፒዩተርና ስልክ በአካባቢያችን ካሉ የኤሌክትሮኒክስ መሸጫ ሱቅ ገዝተው ይጠቀማሉ፡፡ የተለያዩ ተቋማትና ድርጅቶችም የመረጃና ቴክኖሎጂ ግብአቶችን ይጠቀማሉ፡፡

- ተማሪዎች! የሚከተሉትን የቴክኖሎጂ ውጤቶችና የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች አስተውሉ
- ሬዲዮና ቴሌቪዥን፡- የዓለም ወቅታዊ መረጃዎችን ለማዳመጥና ለመመልከት እንዲሁም ለመዝናኛ አገልግሎት ይውላሉ፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



- **ተንቀሳቃሽ ስልክ ፡-** በተለያዩ ቦታ የሚገኙ ሰዎች በድምፅና በምስል እንዲገናኙ በፍጥነት መረጃ እንዲለዋወጡ ያስችላል።
- **ኮምፒዩተር፡-** መረጃ ለማግኘት ለመተንተን፣ ለማቀነባበር፣ ለማስቀመጥና ለመላክ የሚጠቅም የመረጃና ቴክኖሎጂ ግብአት ነው።
- **ፍሪጅ፡-** አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ሥጋ፣ ወተትና የመሳሰሉ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶች ሳይበላሹ እንዲቆዩ ለማድረግና ለማቀዝቀዝ ይጠቅማል።
- **የኤሌክትሪክ ምድጃ፡-** የኤሌክትሪክ ጉልበትን በመጠቀም የተለያዩ ምግቦችን በፍጥነት ለማብሰል ይጠቅማል።
- **የኤሌክትሪክ ጉልበት ማመንጫ ሞተር (ጀኔሬተር)፡-** የኤሌክትሪክ ጉልበትን ለማመንጨት፣ ለመብራትና ማሽኖችን ለማንቀሳቀስ ይጠቅማል።

## መልመጃ 4.1

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ**

1. የግልንጽሕና መጠበቅ ከበሽታ ይከላከላል፡፡
2. አንድ ሰው በአንድ ምሽት ሦስት ሰዓት ብቻ ቢተኛ ለጤናው በቂ ነው፡፡
3. ሰውነታችንን በየጊዜው የምንታጠበው የግልንጽሕናን ለመጠበቅ ነው፡፡
4. ንጹሕ ልብስ መልበስ ያስደስታል፡፡
5. በትምህርት ቤታችን የተለያዩ የማኅበረሰብ አባላት አሉ፡፡

**ለ. በ "ሀ" ሥር ለተዘረዘሩ የቴክኖሎጂ ዉጤቶች በ"ለ"ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ቴሌቪዥን | ሀ. ምግብ ለረጅም ጊዜ ማቆትያ |
| 2. ተንቀሳቃሽ ስልክ | ለ. ምስልና ድምጽ መረጃ መስጫ |
| 3. ፍሪጂ | ሐ. ምግብ ማብሳያ |
| 4. የኤሌክትሪክ ምድጃ | መ. ሰዎችን ዕርሰ በዕርስ ማጋናኛ |
| 5. ኮምፒወተር | ሠ.መረጃ ማቀናበርና መተንተን |

**ሐ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ፡፡**

1.ሰዎች በየጊዜው ሰውነታቸውን ለምን ይታጠባሉ?

ሀ. እንዳያረጁ  ለ. ለመወፈር

ሐ. ጤና ለመጠበቅ  መ. ሁሉም

2. ፓርክ ምን አገልገሎት ይሰጣል?

ሀ. የመዝናኛ አገልግሎት ለ. የመጫወቻ አገልግሎት

ሐ. የጉብኝት አገልግሎት መ. ሁሉም

3. የውኃና ፍሳሽ ሠራተኛ ምን አገልግሎት ይሰጣል?

ሀ. የመጠጥ ውኃ አገልግሎት

ለ. የወተት ስርጭት አገልግሎት

ሐ. የመንገድ ሥራ አገልግሎት

መ. ሁሉም

4. አንድ ቤተሰብ አካላዊ እንቅስቃሴ የሚያደርገው ለምንድን ነው?

ሀ. ሰውነትን ለማድከም ለ. ለንቁ አካል

ሐ. በሽታ ለማምጣት መ. ሁሉም

5. ምግብና መጠጥ ለረጅም ጊዜ ሳይበላሽ እንዲቆይ የሚረዳው የቱ ነው?

ሀ. የኤሌክትሪክ ምድጃ ለ. ፍሪጅ

ሐ. ጀኔሬተር መ. ካርቶን

## መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ከአካባቢያቸው እንዴት ያገኛሉ?

2. ጤነኛ ቤተሰብ መሆን ጥቅሙ ምንድን ነው?

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# 4.2. በትምህርት ቤት ተግባራትን በጋራ ማከናወንና የአቻ ግንኙነትን ማዳበር

## ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- የአቻ ግንኙነትን በማዳበር በትምህርት ቤት የተለያዩ ተግባራትን ታከናውናላችሁ
- የትምህርት ቤት ደንቦችንና መመሪያዎችን ታከብራላችሁ::

**ቁልፍ ቃላት**

- አቻ ግንኙነት
- በጋራ ማከናወን
- ሕግና ደንብ

## ሀ. መሥራት የሚችሉትን ተግባራት ማከናወንና ጨዋታ







ሥዕል.4.10. ተግባርን በጋራ ማከናወን

ተማሪዎች በስፖርት ሲሳተፉ፣ በሰንደቅ ዓላማ ሥነ ሥርዓት ላይ ብሔራዊ መዝሙር ሲዘምሩ፣ ችግኝ ሲተክሉ፣ በክፍል ውስጥ በቡድን የክፍል ሥራ ሲሠሩና የተለያዩ ጨዋታዎች እንደ ኸዋኸዌ፣ ድብብቆሽ፣ አባሮሽ፣ ሱዚ፣ ኳስና የቃላት ውድድር (እስፔሊንግ) ሲጫወቱ በጋራ የአቻ ግንኙነት አደረጉ ማለት ነው።

በተመሳሳይ ዕድሜ ክልል ያሉ ልጆች ወይም ጎልማሶች አብረው ሲሆኑና በጋራ የተለያየ ሥራ ሲሠሩ፣ ጓደኝነት ሲፈጥሩና ሲጫወቱ አቻ ግንኙነት ይባላል። ከዚህም ሌላ ሁለትና ከዚያ በላይ ሆናችሁ ልዩ ልዩ ሥራዎች በአንድ ላይ ስትሠሩ ሥራን በጋራ ማከናወን ወይም በጋራ መሥራት ይባላል። ለምሳሌ፦ በቡድን ስትደንሱ፣ ስታጨበጭቡ፣ የዓባይ ቦንድ ስትገዙ፣ በክበብ ውስጥ ስትሳተፉ፣ አፍና አፍንጫችሁን በማስክ ስትሸፍኑና የመሳሰሉትን ስታከናውኑ በጋራ መሥራት ይባላል።

## የቡድን ሥራ 9

ዓላማ፡መሥራት የሚችሉትን ተግባራት ማከናወን ጨዋታዎችን መለየትና መመደብ

መመሪያ፡-በተግባር ሥዕል 4.10 በቀረቡት የቡድን ሥራዎች መሠረት በጋራ የምትሠሯቸውን ነገሮችና ጨዋታዎችን በሠንጠረዥ ዘርዝሩ። መልሱን ለመምህራችሁ አሳዩ።

| ተ.ቁ. | በጋራ የሚሠሩ ሥራዎች | የጨዋታ ዓይነቶች |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |

ተማሪዎች!አቻ ግንኙነትና በጋራማከናወን ምን ማለት እንደሆነ መልሱን ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ለ. የትምህርት ቤት ሕግና ደንብ

ተማሪዎች! አንደኛ ክፍል እያላችሁ ስለ ትምህርት ቤት ሕግና ደንቦች ተምራችኋል። አስታወሳችሁ? እስቲ የትምህርት ቤት ሕግና ደንቦችን ለመምህራችሁ ተናገሩ።




ሥዕል.4.11. የትምህርት ቤት ሕግና ደንብ

የትምህርት ቤት ሕግና ደንብ የትምህርት ቤት ማኅበረሰብን ሥራ በአግባቡ ለማከናወን ይረዳሉ። መምህራንና ተማሪዎች በእነዚህ ሕግና ደንብ መሠረት ይመራሉ። ለምሳሌ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ማርፈድ የለባቸውም። የደንብ ልብስ ያለበሰ ተማሪ የትምህርት ቤት ደንብና ሕግ አላከበረም። በተቃራኒው ደግሞ ትምህርት ቤት በሰዓቱ የሚገኙ፣ የደንብ ልብስ የለበሱ፣ መምህር ሲያስተምር ክፍል ውስጥ የማይረብሹ ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ሕግና ደንብ ያከበሩ ናቸው።

የትምህርት ቤት ሕግና ደንቦች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ።

- የትምህርት መሣሪያዎችን አሟልቶ በአግባቡ መያዝ
- የትምህርት ሰዓትን አክብሮ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት
- የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ መልበስ
- ትምህርትን በአግባቡ መከታተል
- በክፍልም ሆነ በቅጥር ግቢ ውስጥ አለመረበሽ
- የክፍልና የቤት ሥራዎች በወቅቱ መሥራት
- የትምህርት ቤትን ንብረት መጠበቅና መንከባከብ
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አለመጣላት፣ አለመደባደብ
- መምህራንንና የአስተዳደር ሠራተኞችን ማክበር

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## የቡድን ውይይት 10

ዓላማ: የትምህርት ቤት ሕግና ደንብ መለየት

መመሪያ: በቡድን በመሆን የመወያያውን ነጥብ መሠረት በማድረግ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ::

የትምህርት ቤታችሁን ሕግና ደንቦች ዘርዝሩ::

## መልመጃ 4.2

ሀ.የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ “ሐሰት” በማለት መልሱ

1. በሁለት ልጆች መካከል የሚደረግ ጨዋታ የአቻ ግንኙነት ይባላል::
2. ብቻዋን ቁጭ ብላ የክፍል ሥራ የምትሠራ ተማሪ የአቻ ግንኙነት አድርጋለች::
3. ብዙ ልጆች በትምህርት ቤት ግቢ አበባ መትከላቸው ሥራን በጋራ ማከናወን ነው::
4. የአንድ ክፍል ተማሪዎች ለዓባይ ግድብ ቦንድ መግዛት ሥራን በጋራ ማከናወን ይባላል::
5. በሰንደቅ ዓላማ ሥነ-ሥርዓት ላይ ብሔራዊ መዝሙር መዘምር  ሕግና ደንብ አለማክበር ነው::

## ለ. በ "ሀ" ሥር የቀረቡትን በ "ለ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አቻ ግንኙነት | ሀ. የትምህርት ቤትን ሥነ-ሥርዓት ማክበር |
| 2. በጋራ ማከናወን | ለ. አባሮሽ ጨዋታ |
| 3. ሕግና ደንብ | ሐ. በዕድሜ ተመጣጣኝ የሆኑ ልጆች |
| | መ. የክፍል ሥራን በቡድን መሥራት |

## ሐ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ

1. ሁለት ሰዎች በጋራ ሥዕል ቢሠሩ ምንን ያመለክታል?

   ሀ. ሕግና ደንብ ለ. በጋራ ማከናወን

   ሐ. ማኅበረሰብ መ. ሁሉም

2. ሁለት ልጆች በአንድ ላይ የካርቶን አሻንጉሊት መሥራት ምንን ያመለክታል?

   ሀ. በጋራ ማከናወን ለ. ቀልድ መቀለድን

   ሐ. ሕግና ደንብ ማክበርን መ. ሮቦትን ማሳቅ

3. የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ አለመልበስ ምን ያመለክታል?

   ሀ. ቤተሰብን አለማክበር

   ለ. የትምህርት ቤት ደንብ አለማክበር

   ሐ.ጓደኛን አለማክበር

   መ. ፖሊስን አለማክበር

4. አንድ ሰው ብቻውን መሥራት የማይችለውን ሥራ__________ ይኖርበታል፡፡
   ሀ. በመተባበር ማከናወን ለ. በጋራ ማከናወን
   ሐ. በእርዳታ ማከናወን መ. ሁሉም

**መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. አቻ ግንኙነት ምን ማለት ነው?
2. በጋራ ማከናወን ምን ማለት ነው?
3. ከትምህርት ቤታችሁ ሕግና ደንብ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡

# 4.3 ንጽሕናና የግል ጤና

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ :-**

- የራሳችሁንና የትምህርት ቤታችሁን ጽዳት ትጠብቃላችሁ

## ሀ.የራስንና የትምህርት ቤትን ጽዳት እንዴት እንጠብቃለን?

ተማሪዎች! ከዚህ በፊት ባለው የትምህርት ክፍል ስለግል ንጽሕና ምንነት ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ስለግል ንጽሕናችሁ አጠባበቅ ትማራላችሁ፡፡የግል ንጽሕናችሁን እንዴት ትጠብቃላችሁ? የትምህርት ቤታችሁንስ ጽዳት እንዴት ትጠብቃላችሁ? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource





ሥዕል.4.12 የግል ንጽሕና አጠባበቅ

የግል ንጽሕና ሲባል ዘወትር የሰውነታችንን፣ የፀጉራችንና የምንለብሳቸውን ልብሶች ንጽሕና መጠበቅ ማለት ነው፡፡ የተሟላ ጤንነት እንዲኖረን ንጽሕናችንን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡

የግል ንጽሕናን መጠበቅ የተለያየ ጥቅሞች ይሰጣል፡፡

ለምሳሌ ፡- በሽታን መከላከል፣ ንቁ ደስተኛና ጤነኛ ለመሆን እንዲሁም ሥራን በትጋት ለመሥራት ይጠቅማል፡፡

በተቃራኒው ደግሞ የግል ንጽሕ አለመጠበቅ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ፡- ሰውነት መጥፎ ጠረን ይኖረዋል፤ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብቶ የመሥራት ሁኔታን ይቀንሳል፤ ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል፤ የተለያዩ ተባዮች በፀጉራችንና ልብሳችን ውስጥ እንዲፈጠሩ መንስኤ ይሆናል፡፡

በንጽሕና ጉድለት ለሚመጡ እንደ እከክ፤ ትራኮማ፤ ወስፋት፤ ኮሌራ፤ ለመሳሰሉት በሽታዎች ተጠቂ ያደርጋል፡፡

የትምህርት ቤት አካባቢዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ጽዱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የትምህርት ቤታችሁ ቅጥር ግቢ፣ የመማሪያ

ክፍሎች፣ ቤተ-መጻሕፍት፣ ቢሮዎች፣ የመጸዳጃ ቤቶች፣ የመመገቢያና የመጫወቻ ቦታዎች ሁሉ መጽዳት ይኖርባቸዋል:: ይህ በመሆኑ የግል ጤናችን ከተጠበቀ ትምህርታችንን በጥሩ ሁኔታ እንከታተላለን፤ ደስተኞች እንሆናለን::

ከዚህ ቀጥሎ የንጽሕና መስጫ ቁሳቁሶችና አጠቃቀማቸውን እንመለከታለን

## የግል ንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች፤

- **የፀጉር ማበጠሪያ:-** በተለያየ ቅርጽና መጠን የተሠሩ ሆኖ ፀጉርን ለማበጠርና ንጽሕናውን ለመጠበቅ ይጠቅማል::
- **የገላ ሣሙናና ሻምፑ:-** ገላና ፀጉር ለማጽዳት ይጠቅማሉ::
- **የጥፍር መቁረጫ:-** ጥፍራችን ሲያድግ በውስጡ ቆሻሻ ስለሚይዝ በየጊዜው ጥፍራችንን ለመቁረጥ ይጠቅማል::
- **የጥርስ ማጽጃ:-** የጥርስ ብሩሽና የጥርስ ሣሙና (ለምሳሌ:- ኮልጌት) ጥርሳችንን ለማጽዳት ያገለግላል::
- **ንጹሕ ፎጣ :-** ፊትንና ገላን ስንታጠብ ለማጽጃና ለማድረቂያ ያገለግላል
- **የልብስ ሣሙና:-** በፈሳሽ ፣ዱቄትና ጠጣር መልክ ይገኛል: : ልብስ ለማጠብ ይጠቅማል::
- **ካውያ:-** የተጨማደደን ልብስ አስተካክሎ ለመተኮስ እንጠቀማለን::

# የቤትና የግቢ ማጽጃ ቁሳቁሶች፤

- **የወለል ማጽጃ ፡-** መወልወያ፣ የበርኖስ ቁራጭ ሰምና መጥረጊያ
- **የመጸዳጃ ቤት ማጽጃ፡-** ፈሳሽ ኬሚካሎች፣ ቪም፣ ብሩሽና ስፖንጅ
- **የወለል ምንጣፍ ማጽጃ፡-** የወለል ምንጣፍ መፈግፈጊያ እና ብሩሽ
- **የኮርኒስና የግድግዳ ማጽጃ ፡-** ረጅም እጀታና ጫፉ ላይ መጥረጊያ ያለው ማጽጃ
- **የመስኮትና መስተዋት ማጽጃ ፡-** ፈሳሽ ሣሙና፣ ስፖንጅና መወልወያ ንጹሕ ፎጣዎች
- **የምግብ ማብሰያ ዕቃዎች ማጽጃ ፡-** የዕቃ ማጠቢያ ሣሙና፣ ስፖንጅ፣ ሽቦና ንጹሕ ፎጣ
- **ቅጥር ግቢን ማጽጃ ፡-** መጥረጊያ፣ የአትክልት መቁረጫ መቀስ፣ የውኃ ባልዲ፣ የአትክልት ውኃ ማጠጫ ጎማና የሣር ማጨጃ ማሽን




ሥዕል4 .13 የቤትና የግቢ ጽዳት መስጫ ቁሳቁሶች

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



### የቡድን ውይይት 11

**ዓላማ:- የግል ንጽሕና መጠበቂያና የትምህርት ቤት የጽዳት ዕቃዎች መለየት**

**መመሪያ:- በሥዕል 4.13. መሠረት በቡድን በመሆን የሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ።**

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

**የግል ንጽሕና መጠበቂያና የትምህርት ቤት ማጽጃ ቁሳቁሶች ስማቸውን በመለየት ዘርዝራችሁ ጻፉ።**

ተማሪዎች! ሥዕሉን ተመልክታችሁ የግልና ንጽሕና መስጫና የቤትና የግቢ ቁሳቁሶች በቀላሉ መለየት ትችላላችሁ።

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## መልመጃ 4.3

**ሀ.የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ “ሐሰት” በማለት መልሱ::**

1. ፀጉራችንን በመታጠብ የግል ንጽሕናችንን እንጠብቃለን::
2. በትምህርት ቤት ውስጥ የመማሪያ ክፍሎችን ማጽዳት የግል ጤናችንን መጠበቅ ማለት ነው::
3. የቆሸሸ ልብስ መልበስ የንጽሕና ዓይነት ነው::
4. የትምህርት ቤታችሁን ቅጥር ግቢ ማጽዳት ለጤና ጥሩ ነው::
5. የራሳችሁና የትምህርት ቤታችሁ ጽዳት ጤነኛ እንድትሆኑ ያደርጋል::

**ለ. በ “ሀ” ሥር የቀረቡትን በ “ለ” ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ::**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የገላ ሳሙና | ሀ. ለገላ ማድረቂያ |
| 2. ካውያ | ለ. ጥርስን ለማፅዳት |
| 3. የጥርስ ቡሩሽ | ሐ. የተጨማደደ ልብስን ለመተኮስ |
| 4. ንፁህ ፎጣ | መ. ለገላ መታጠቢያ |

**ሐ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ::**

1.የራሳችሁን ጤና ለመጠበቅ___________ማድረግ አለባችሁ::

ሀ. ገላ መታጠብ ለ. ፀጉር መታጠብ

ሐ. ንጹሕ ልብስ መልበስ መ. ሁሉም

2.የመማሪያ ክፍሎች ለምን ይጸዳሉ?

ሀ. በሽታ ለማስተላለፍ ለ. በሽታ ለመከላከል

ሐ. ክፍሉን ለማስፋት መ. ከቅጣት ለመዳን

3.ከሚከተሉት አንዱ በግል ንጽሕና ውስጥ አይመደብም::

ሀ. ቢሮ ማጽዳት ለ. ሽንት ቤት ማጽዳት

ሐ. መኪና ማጽዳት መ. መልሱ አልተሰጠም

4.ገላን መታጠብና ጥርስን ማጽዳት ምን ተብሎ ሊጠራል ይችላል?

ሀ. አጣቢነት ለ. የአካባቢ ንጽሕና

ሐ. የግል ንጽሕና መ. ሠራተኛ

5.ንጽሕናውን የማይጠብቅ አካል ምን ሊያጋጥመው ይችላል?

ሀ. ጤና ለ. በሽታ ሐ. ፍርሐት መ. ኪሣራ

**መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. የግል ንጽሕናን መጠበቅ ምን ጥቅም ያስገኛል?
2. የትምህርት ቤት ጽዳት መጠበቅ ጥቅሙ ምንድን ነው?

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

- ማኀበረሰባዊ አካባቢ ሰዎችና በአቅራቢያቸው ያሉ ነገሮችን እንደ ሕንፃዎች፣ ፋብሪካዎች፣ መንደሮች፣ ሱቆችና የመሳሰሉትን አካላትን ያካትታል።
- የግል ንጽሕናን መጠበቅ ከበሽታ ይከላከላል፤ ጤናማም ያደርጋል።
- እንያንዳንዱ ቤተሰብ አባል የተለያየ ፍላጎት ይኖረዋል፤ የምግብ፣ የልብስ፣ የመጠለያ፣ የስልክ፣ የትምህርትና የሽርሽር ፍላጎት ይኖረዋል።
- የቤተሰብ አባላት ከመሠረታዊ የሰው ልጆች ፍላጎት ውጪ የተለያየ ሌሎች ፍላጎቶች ይኖራቸዋል።
- በትምህርት ቤትና በዙሪያው ያሉ ማኀበረሰቦች ፍላጎታቻቸውን በተለያየ መንገድ ያሟላሉ። ትምህርት ቤት ውስጥ በክበብ የመሳተፍ ፍላጎት ፤ በአካባቢው ደግሞ የውኃና ፍሳሽ አገልግሎት ፍላጎት ይኖራል።
- በዙሪያችን ሬዲዮ፣ ማቀዝቀዣ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ እና የመሳሰሉት የተለያዩ የመረጃና ቴክኖሎጂ ግብአቶች ከተቋማትና ከድርጅቶች በግዢ ይገኛሉ።
- በሙዚቃ ክበብ፣ በስፖርት ክበብ፣ በችግኝ ተከላና በልዩ ልዩ ጨዋታዎች መሳተፍ የአቻ ግንኙነትን ያዳብራል።
- የትምህርት ቤት ማኀበረሰብ፤ የትምህርት ቤትን ሕግና ደንብ ያከብራሉ።
- የንጽሕናና የግል ጤና አጠባበቅ ዘዴ ጤናማ ማኀበረሰብን ይፈጥራል።

# የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ.የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. ፀጉር ያለመታጠብና የቆሸሸ ልብስ መልበስ የግል ንጽሕና ይባላል::
2. አንድ ቤተሰብ የራሱን ፍላጎት በሚፈልገው መንገድ ማሳካት ይችላል::
3. ተማሪዎች የትምህርት ፍላጎታቸውን በትምህርት ቤታቸው ሊያገኙ ይችላሉ::
4. ቴሌቪዥን ከመረጃ ቴክኖሎጂዎች ዓይነት አንዱ ነው::
5. በትንሿ ሉሊትና በአቶ በቀለ መካከል የአቻ ግንኙነት ሊፈጠር ይችላል::

**ለ. በ "ሀ" ሥር የቀረቡትን በ "ለ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ::**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ቤተሰብ | ሀ. ወላጅ ያጡ ልጆችን መርዳት |
| 2. የግልንጽሕና | ለ. በቤተ መጻሕፍት ፀጥታ ማክበር |
| 3. አቻ ግንኙነት | ሐ. እናት፣ አባትና ልጆች |
| 4. በጋራ ማከናወን | መ. በተመጣጣኝ ዕድሜ ክልል ያሉ ልጆች |
| 5. ሕግና ደንብ | ሠ. ገላን መታጠብ፣ ልብስን ማጠብ |
| | ረ. ከመጠን በላይ መብላት |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ::**

1.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ማኅበራዊ አካባቢን አይገልጽም::

ሀ. መንደር  ለ. ሕንፃ  ሐ. ሆቴል  መ. እርሳስ

2. በአካልና በአእምሮ የታመመ ምን ተብሎ ሊጠራ ይችላል?

ሀ. ደስተኛ  ለ. ሐዘንተኛ  ሐ. ሕመምተኛ  መ. ጤነኛ

3. ዘወትር ፀጉርን መታጠብና ልብስን ማጠብ ምን ይባላል?

ሀ. ልብስ ማቆሸሽ  ለ. ስንፍና ማብዛት

ሐ. የግል ንጽሕና መጠበቅ  መ.ሁሉም መልስ ነው

4. ከሚከተሉት አንዱ የቤተሰብ ፍላጎት አይደለም::

ሀ.ገንዘብ ማስቀመጥ  ለ. ልጆችን መንከባከብ

ሐ.ፍቅር መስጠት  መ. አካባቢን መረበሽ

5. በትምህርት ቤት ዙሪያ ያሉ የአንድ አካባቢ ማኅበረሰብ አባላት ፍላጎታቸውን ለማሳካት ከትምህርት ቤቱ ምን ያገኛሉ?

ሀ. ዳቦና ሻይ

ለ. ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ማስገባት

ሐ. የስልክ አገልግሎት

መ. ስኳርና ዘይት

6. ከሚከተሉት አንዱ የመረጃ ቴክኖሎጂ ግብአት ነው፡፡

ሀ. ስልክ ለ. ኮምፒዩተር ሐ. ሬዲዮ መ. ሁሉም

7. ሁለት መምህራን አንድ ክፍል ያስተምራሉ፤ አብረውም ይጫወታሉ፤ይህ ምንን ያመለክታል?

ሀ. በጋራ ማከናወን ለ. መጠላላትን

ሐ. የአቻ ግንኙነትን መ. መፈራራትን

8. በትምህርት ቤት ሕግና ደንብ መሠረት ስሕተት የሆ ነው የቱ ነው?

ሀ. አለማርፈድ ለ. የግል ንጽሕና መጠበቅ

ሐ. የክፍልን ንጽሕና አለመጠበቅ መ.ሁሉም መልስ ናቸው

9. የቤተሰብ ጤናን መጠበቅ ምን ጠቀሜታ አለው?

ሀ. ደስተኛ ያደርጋል ለ. ንቁ ሠራተኛ ያደርጋል

ሐ. ከበሽታ ነፃ ያደርጋል መ. ሁሉም መልስ ነው

10. የትምህርት ቤታችሁን ጽዳት እንዴት መጠበቅ ይቻላል?

ሀ. ቆሻሻን ቶሎ ቶሎ አለማጽዳት

ለ. የመማሪያ ክፍሎችን አለመጥረግ

ሐ. ቅጥር ግቢውን ሁሉ በማጽዳት

መ. ወረቀትና ፒላስቲክ በየቦታው በመጣል

## መ. በክፍት ቦታዎች ላይ ትክክለኛውን መልስ ሙሉ።

1. በአካሉና በአእምሮው ላይ ምንም ሕመም የሌለው ቤተሰብ ___________ይባላል።
2. አንድ ተማሪ በራሱ ተነሣሽነት የሚፈልገውን ነገር በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያገኝበት ሁኔታ____________ይባላል።
3. የኤፍ. ኤም ሬዲዮዎች የ___________ግብአት ናቸው።
4. በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የ_________ ግንኙነት አላቸው
5. የትምህርት ቤቱን አበባ የቀጠፈ ተማሪ በትምህርት ቤቱ ____________ይቀጣል።

## ሠ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ።

1. የግል ንጽሕና ምን ምን ነገሮች እንደሚያካትት ዘርዝሩ።
2. የቤተሰብ ጤና መጠበቅ ለምን ይጠቅማል?
3. በትምህርት ቤት የሚገኙ የማኅበረሰብ አባላትን ዘርዝሩ።
4. የአቻ ግንኙነት ማለት ምን ማለት ነው?
5. በትምህርት ቤታችሁ ከሚገኙ ሕግና ደንቦች ሦስቱን ጥቀሱ።

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# ፍተሻ

ልታከናውኗቸው የምትሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሣጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ፡፡

1. የግል ንጽሕና መጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ እገልጻለሁ፡፡ ☐
2. የቤተሰብ ጤና ለመጠበቅ የንጽሕና ጠቀሜታ፤ እንቅስቃሴና ዕረፍት እንደሚያስፈልግ አስረዳለሁ፡፡ ☐
3. የቤተሰብ አባላትና ፍላጎታቸውን አስረዳለሁ፡፡ ☐
4. የመረጃና ቴክኖሎጂ ፋሲሊቲ/ግብአት የት እንደሚገኝ እዘረዝራለሁ፡፡ ☐
5. በትምህርት ቤትና በአካባቢው የሚገኙ የማኅበረሰብ አካላትን ፍላጎትን እለያሁ፡፡ ☐
6. የአቻ ግንኙነትን በማዳበር በትምህርት ቤት የተለያዩ ተግባራት ማከናወን እንደሚቻል እናገራለሁ፡፡ ☐
7. የትምህርት ቤት ደንቦችና ሕጎች ማክበር እንደሚያስፈልግ አስረዳለሁ፡፡ ☐

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# ምዕራፍ አምስት
# ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች

ከምዕራፉ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር በቃት

ይህን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የመገናኛና ቴክኖሎጂ መረጃዎችን በማየትና በመጠቀም የትራፊክ ደንቦችን ትገልጻላችሁ
- ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በሕፃናት ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ትለያላችሁ
- ኤች.አይ.ቪ.በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት ኀዘኔታና ፍቅር ታሳያላችሁ

## የምዕራፉ ይዘቶች

5.1.የመንገድ ደኅንነት

5.2.ኤች.አይ.ቪ. / ኤድስ

# 5.1. የመንገድ ደኅንነት


ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የትራፊክ ደንቦችን ትግልጻላችሁ
- የትራፊክ ደንቦችን ትተገብራላችሁ
- የመገናኛና ቴክኖሎጂ መረጃዎችን በማየትና በመጠቀም የትራፊክ ደንቦችን ትገልጻላችሁ

**ቁልፍ ቃላት**

☞ የትራፊክ ደንቦችን

**የመንገድ ደኅንነት ምን ማለት ነዉ ?**



ሀ ለ


ሥዕል 5.1 የመንገድ ደኅንነት

ከላይ ያለውን ሥዕል 5.1 በማየት የመንገድ ደኅንነት ያለው የትኛው መንገድ ነዉ? የሌለውስ የትኛው መንገድ ነው?

የመንገድ ደኅንነት በመንገድ ተጠቃሚዎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን የሞት ወይም ሌሎች አደጋዎችን መጠን ያሳየናል።

1. መሠረታዊ ትራፊክ ደንቦች

መሠረታዊ ትራፊክ ላይ ደንቦች ምንድን ናቸው?



ሥዕል 5.2 የመንገድ ላይ ደንብ

ከላይ ካለው ሥዕል ላይ የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**የቡድን ውይይት5.1**

ዓላማ:- መሠረታዊ የመንገድ ላይ ደንቦችን መጠየቅ

መመሪያ:- በቡድን በመሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሠርታችሁ ለመምህራችሁ ግለጹ።

በእግረኛ መንገድ ላይ በግራ መስመር ስትጓዙ ተሽከርካሪዎች የሚመጡት ከፊት ለፊትታችሁ ወይስ ከጀርባችሁ ነው?


ተሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ ሲሽከረከሩ የሚጓዙት በአንድ አቅጣጫ ቀኝ መስመራቸውን ይዘው ነው። ስለዚህም እግረኞች ሲጓዙ ግራ መስመራቸውን መያዝ አለባቸው። ይህ ደግሞ በመንገድ ላይ ከፊት ለፊታቸው የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን በቀላሉ ለማየት ያስችላቸዋል።

አሽከርከዎች ሲያሽከረክሩ ፍጥነታቸውን በመቆጣጠር፣ ለእግረኛ ቅድሚያ በመስጠት፣ ለራሳቸው እና ለእግረኛው ጥንቃቄ ማድረግ

ይኖርባቸዋል፡፡ እግረኞች መንገድ ሲያቋርጡ በትክክለኛ ማቋረጫ መንገድ ማቋረጥ ይገባቸዋል፡፡ ተማሪዎች! በምትንቀሳቀሱበት ጊዜ የሚከተሉትን መሠረታዊ የመንገድ ደንቦችን መከተል ይገባችኋል፡፡

## ሀ.የእግረኛ ማቋረጫ መስመር

ተማሪዎች! ሰዎቹ በየትኛው የትራፊክ መንገድ እያቆረጡ ነው?



ሥዕል 5.3 የእግረኛ ማቋረጫ መስመር

ከላይ ካለዉ ሥዕል ላይ የተረዳችዉትን ለመምህራቹ ንገሩ

**የተግባር ሥራ 1**

ዓላማ ፡- የእግረኛ ማቋረጫ ምልክትን መለየት

መመሪያ፡-ተማሪዎች ከታችን ያለው ጥያቄ ሠርታችሁ አሳዩ

- የእግረኛ መንገድ ማቋረጫ መስመር በወረቀት ላይ ሣሉ

የእግረኛ ማቋረጫ መስመር እግረኞች መንገድ የሚሻገሩበት የጥቁርና ነጭ ቀለም መስመሮች ናቸው። ሕጻናት የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ ሲያቋርጡ ከአዋቂ ሰዎች ጋር መሆን አለባቸው። በቀለበት መንገድ ላይ የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ ስለሌለ በቀለበት ድልድይ እንሻገራለ።

## ለ.የትራፊክ መብራት ደንቦች

የትራፊክ መብራት ምን ማለት ነው ?

**የሚና ጫወታ**

መመሪያ፦ በክፍል ዉስጥ በቡድን በመሆን የሚናጫወታ ተጫወቱ።

ከቡድናችሁ አንዱ ትራፊክ ፖሊስ ሌላው ደግሞ የመኪና አሽከርካሪ (ሾፌር) በመሆን እየተለዋወጣችሁ ተጫወቱ።

- ትራፊኩ ቀይ መብራት ምልክት ሲያሳይ ማሽከርከራችሁን ታቆማላችሁ። ቢጫ የመብራት ምልክት ሲያሳይ ለመንቀሳቀስ ትዘጋጃላችሁ። አረንጓዴ የመብራት ምልክት ሲያሳይ መንቀሳቀስ ትጀምራላችሁ።




ሥዕል 5.4 የትራፊክ መብራት

## የቡድን ውይይት 5.2

ዓላማ-የትራፊክ መብራት ደንቦችን መለየት

መመሪያ በአነስተኛ ቡድን በመሆን በሚከተሉት ጥየቄዎች ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ቀይ የትራፊክ መብራት ሲበራ ምንን ያመለክታል?

ለ. ቢጫ የትራፊክ መብራት ሲበራ ምንን ያመለክታል?

ሐ. አረንገጓዴ የትራፊክ መብራት ሲበራ ምንን ያመለክታል?

መ.የትራፊክ መብራት ደብተራችሁ ላይ በመሣል አሳዩ፡፡

የትራፊክ መብራት በመንገዶች ላይ የተሽከርካሪዎችንና የእግረኞችን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር ምልክት ነው፡፡ የትራፊክ መብራት ሦስት የተለያዩ ቀለሞች ያሉት ነው፡፡ እነሱም አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ናቸው፡፡ ቀይ የትራፊክ መብራት ሲበራ ለተሽከርካሪ "ቁም" ማለት ሲሆን ለእግረኛ ደግሞ እለፍ ማለት ነው፡፡ ቢጫ የትራፊክ መብራት ሲበራ ለተሽከርካሪ "ተዘጋጅ" እና አረንጓዴ የትራፊክ መብራት ሲበራ ለተሽከርካሪ "ሂድ" ማለት ሲሆን ለእግረኛ ደግሞ "ቁም" ማለት ነው፡፡

## ሐ.የትራፊክ ምልክት

ተማሪዎች! በመንገድ ላይ የተተከሉ የተለያዩ የትራፊክ ምልክቶችን አስተውላችኋል?




ሥዕል 5.5 ትራፊክ ምልክት

ከላይ ካለው ሥዕል ላይ ምንን የተረዳችሁት ለመምህራችሁ ንገሩ።

**የቡድን ውይይት 5.3**


ዓላማ:- የትራፊክ ምልክት ደንቦችን መለየት

መመሪያ:- ተማሪዎች በቡድን ሆናችሁ የሚከተሉትን የትራፊክ ምልክቶች በሥዕል 5.5 መሰረት ተመልክታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ግለፁ።

- የመንገድ ዳር ትራፊክ ምልክቶች፦ በመንገድ ዳር የሚተከሉ የተሽከካሪዎችንና የእግረኞችን የመንገድ አጠቃቀም የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው።

## 2. በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎች

በተሽከርካሪ መንገድ ላይ የሚደርሱ አደጋዎች ምንድን ናቸው?



ሥዕል 5.6 በተሽከርካሪዎች የደረሱ የትራፊክ አደጋዎች

ከላይ ባለው ሥዕል ላይ የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## የቡድን ዉይይት 5.4

ዓላማ፡- በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎችን መለየት

መመሪያ፡- በአነስተኛ ቡድን በመሆን በሚከተሉት ጥየቄዎች ላይ ተወያይመታችሁ ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡

- በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን በተሽከርካሪ ምክንያት የሚደርሱ አደጋዎች ምን ምን ስምታችኋል?

በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ የትራፊክ አደጋዎች፡-

- የሞት፣ የአካል ጉዳት

  ለምሳሌ፡- የእግርና እጅ መሰበር፣ መቆረጥ

- የንብረት መውደም

  ለምሳሌ፡- የመኪና መገልበጥ


- የቤተሰብ መበተን

  ለምሳሌ፡- የልጆች ያለአሳዳጊ መቅረት

ተማሪዎች! በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎች በጣም አሰቃቂና ዘግናኝ ናቸው፡፡ ስለዚህ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱና ስትመለሱ የተማራችሁትን መሠታዊ የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በማስተዋል መጓዝ ይኖርባችኋል፡፡

## ሀ. በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎችና መንስኤዎች

በተሽከርካሪዎች አማካኝነት መንገድ ላይ የሚደርስ አደጋ መንሥኤያቸው ምን እንደ ሆነ ተናገሩ፡፡



ሥዕል 5.7 የተሽከርካሪ አደጋዎች መንስኤ

በተሽከርካሪዎች መንገድ ላይ የሚደርሱ ዋና ዋና የአደጋዎች መንስኤዎች፦

- በተከለከለ የቀለበት መንገድ ላይ ማቋረጥ
- ለእግረኞች በተፈቀደ መንገድ ያለማቋረጥ
- የደንነንነት ቀበቶ አለማሰር
- ባልተፈቀደ የባቡር ሀዲድ ላይ ማቋረጥ
- በመኪና መንገድ ላይ መጫወት
- ከተፈቀደ የፍጥነት ወሰን ውጭ ማሽከርከር

ተማሪዎች! በተሽከርካሪዎች መንገድ ላይ የሚደርሱ አደጋዎች መንስኤዎች ተምራችኋል፡፡

ተማሪዎች! የትራፊክ መንገድ ደኅንነትን ማወቅ፤ መጠበቅና በአግባቡ መተግበር ራሳችንን ከአደጋ እንድንጠብቅ ይረዳናል፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## መልመጃ 5.1

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. እግረኛ ሁል ጊዜ የግራ መንገድን ይዞ መጓዝ አለበት።
2. የመኪና መንገድን እግረኞች በእግረኛ ማቋረጫ መስመር ማቋረጥ ይገባል።
3. የትራፊክ መብራት የቀለም ዓይነት ሁለት ናቸው።
4. ልጆች ከአዋቂ ሰው ጋር የመኪና መንገድ መሻገር አለባቸው።
5. ቀይ የትራፊክ መብራት ሲበራ ማንኛውም መኪና አይቆምም።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ጻፉ።**

1. መሠረታዊ የትራፊክ ደንቦችን ዘርዝሩ።
2. በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎችን ዘርዝሩ።
3. በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎች መከላከያ ዘዴዎችን ዘርዝሩ።

# 5.2. ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር በቃት**

**ይህን ንዑስ ርዐስ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡**

- ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በሕፃናት ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ መለየት
- ኤች.አይ.ቪ.. በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት ኀዘኔታና ፍቅር ማሳየት

**ቁልፍ-ቃል**

☞ ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ

## ሀ. የኤች አይ ቪ /ኤድስ በሽታ ምንነት

• ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምንድን ነዉ ?

ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ የሰውነት በሽታ የመከላከል አቅም የሚያዳክም በሽታ ነው።ኤች አይ ቪ/ኤድስ በፍጥነት እየተዛመተ እና የሰውን ልጅ ሕይወት እየቀጠፈ ያለ የሰው ልጆች ጠንቀኛ በሽታ ነው። ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ መድሐኒት የሌለው ገዳይ በሽታ ነው። የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ሕመምተኛ ተገቢውን የህክምና ክትትል እያደረገ እንደ ማንኛውም ጤናማ ሰው የዕለት ተዕለት ሥራውን እየሠራ ረዥም ዓመት መኖር ይችላል።

## ለ. የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች

ተማሪዎች! በሬድዮ ወይም ቴሌቭዥን ስለ ኤች. አይ. ቪ/ ኤ.ድ.ስ. ሲዘመር የምታውቁት መዝሙር መዘመር ትችላላችሁ? የመዝሙሩን ግጥም በቡድን ሆናችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘምሩ።

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## የሚና ጨዋታ

ዓላማ:- ስለ ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ አደገኛ መተላለፍያ መንገዶች አወጋገድ መለየት

መመሪያ:- በአነስተኛ ቡድን በመሆን የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ የሚተላለፍባቸውን አደገኛ ሁኔታ እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል በሚና ጨዋታ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ተማሪዎች! አንዳችሁ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚተላለፍባቸውን አደገኛ መንገዶች ትናገራላችሁ ሌላችሁ እንዴት ማስወገድ እንደሚገባ ትመልሳላችሁ፡፡

ተማሪዎች! መልሳችሁ የሚከተሉትን የሚያካትት ከሆነ ጥሩ ሞክራችኋል፡፡

| ተ.ቁ | ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አደገኛ መተላለፊያ | እንዴት መከላከል እንደሚቻል |
|---|---|---|
| 1 | በደም ንክኪ | ከደም ንክኪ መራቅ |
| 2 | ስለታማ ነገር እንደ ምላጭያሉትን መጠቀም | የግላችንን ስታማ ነገር መጠቀምና የሌሎችን ሰዎች አለመጠቀም |
| 3 | የጥርስ ብሩሽ በጋራ መጠቀም | የራሳችንን ጥርስ ብሩሽ ብቻ መጠቀም |
| 4 | የሕክምና መድሐኒት መስጫ መርፌ በጋራ መጠቀም | የሕክምና መድሐኒት መስጫ መርፌ በጋራ አለመጠቀም |

የኤች አይ ቪ/ኤድስ በደማችን መኖሩ የሚታወቀው በሕክምና ምርመራ ብቻ ነው፡፡

አንድ ሰው ኤች አይ ቪ/ኤድስ በደሙ መኖሩ በሕክምና ከተረጋገጠ ይህ ሰው ኤች አይቪ/ኤድስ ፖዘ ቲቭ ተብሎ ይጠራል፡፡ ኤች አይቪ/ኤድስ፡-ፆታ፣ ዕድሜ፣ የሥራ ሁኔታ፣ ዘርና ቀለም ሳይለይ ማንኛውንም ሰው ይይዛል፡፡ የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ዋና ዋና መተላለፍያ መንገዶች የሚከተለት ናቸው፡፡

- በደም ንክኪ ለምሳሌ፤ የአንድ ሰዉ ደም ከሌላ ሰው ደም ጋር ሲነካካ
- በቫይረሱ የተበከለ ደም ወደ ጤናማ ሰው ደም ሲገባ
- ሕመምተኛው የተጠቀመበትን የጥርስ ብሩሽ ወይም መፋቂያ ጤናማ ሰው ሲጠቀምበት
- ሕመምተኛ የሚጠቀምባቸውን ስለታማ ነገሮች እንደ ምላጭ፣ ቢላዋ፣ ጥፍር መቁረጫ ጤናማው ሰው ሲጠቀምበት
- ሕመምተኛው የሚጠቀምባቸውን የሕክምና ዕቃዎች እንደ መርፌ በጋራ በመጠቀም

### ሐ. የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ የማይተላለፍባቸው መንገዶች

የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ የማይተላለፍባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

**የቡድን ዉይይት 5.5**

ዓላማ:- ኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ የማይተላለፉባቸው መንገዶችን መጠየቅ

መመሪያ:- በቡድን በመሆን የሚቀጥለውን ጥያቄ ሥሩ፡፡

☞ ኤች አይ ቪ ኤድስ የማይተላለፍባቸውን መንገዶች ግለጽ?

ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ በሽታ የማይተላለፍባቸው መንገዶች አብሮ መብላት፣ የጥርስ ቡርሽ በጋራ አለመጠቀም፣ የደም ንክኪ ማስወገድ፣ በመጨባበጥ፣ አብሮ በአንድ ወንበር ላይ በመቀመጥ፣ አብሮ በመጫወትና የመሳሰሉት ናቸው::

## 1.ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በሕፃናት ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ

### የቡድን ሥራ

ዓላማ:- ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በሕፃናት ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ መጠየቅ

መመሪየ ፦በቡድን በመሆን በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::

1. ለምን ሕጻናት ፍቅርና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል ?
2. ሕጻናት በማንኛውም በሽታ ሲታመሙ ምን ያስፈልጋቸዋል?
3. አንድ ሰው ኤች.አይ.ቪ / ኤድስ ሕመምተኛ መሆኑን በምን ይታወቃል?

### ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በሕፃናት ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ፦

ሕጻናት ወላጆቻቸውን በሞት ሲያጡ፣ ፍቅር የሚሰጣቸው ሰው መታጣት፣ የሚንከባከባቸው ሰው እጦት፣ ልብሳቸውን እና ገላቸውን የሚያጥብላቸው ሰው ማጣት፣ በቂ ምግብ እና መጠጥ የሚሰጣቸው ሰው ማጣት፣ የመማሪያ ቁሳቁስ የሚያሟላላቸው ሰው አለመኖር ፣ ከትምህርት ቤት መቅረት፣ አብሮአቸው የሚጫወቱ ሰዎች ማጣት እና የመሳሰሉት ናቸው::

## 2. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት ኀዘኔታና ፍቅር ማሳየት

ተማሪዎች! ወላጆቻችሁ በታመማችሁ ጊዜ ምን አይነት እንክብካቤ ያደርጉላችኋል?

የሚከተለዉን ግለ ታሪክ በቡድን በመሆን በማንበብ ተወያዩ

ወላጆቹን በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያጣ ልጅ

ልጁ ወላጆቹን በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሞት ስላጣ የሚኖረው ከአሳዳጊዎቹ ጋር ነው፡፡ ወላጆቹ ያሳዩት የነበረዉን ፍቅርና እንክብካቤ አሳዳጊዎቹ አይሰጡትም ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ በቂ ምግብና ሕክምናም አያገኝም፡፡ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በደሙ ስላለ እንዳይተላለፍባቸው በማሰብ አብረውት አይበሉም፤ አይጠጡም፤ አይጫወቱም እንዲሁም ሌሎችንም ነገሮች በጋራ አይጠቀሙም፡፡ ይህም በመሆኑ ከትምህርት ቤት በተደጋጋሚ ይቀር ነበር፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች፤**

ተማሪዎች ይህ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደሙ ያለበት ልጅ የክፍላችሁ ተማሪ ቢሆን ምን ታደርጋላችሁ?

አብራችሁ ምግብ ትበላላችሁ? ትጫወታላችሁ?

ደብተራችሁንም ሆነ መጽሐፋችሁን ታውሱታላችሁ?

በድንገት ሲጫወት ቢወድቅ ትረዱታላችሁ?

ማንኛውም ሰው ጥንቃቄ ካላደረገ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሊያዝ ይችላል፡፡ ስለዚህም ማንኛውም ሰው ለሌላው ርኅራሄና ፍቅር ማሳየት፣ እገዛና ትብብር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## መልመጃ 5.2

**ሀ.የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሽታ መድሐኒት የሌለው ገዳይ በሽታ ነው፡
2. የጥርስ ብሩሽን በጋራ መጠቀም ኤች. አይ. ቪ.ን አያስተላልፍም።
3. ሕጻናት በኤች. አይ. ቪ/ኤድስ አይያዙም።
4. የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሕመምተኛን በማየት ማወቅ አይቻልም።
5. ኤች አይ ቪ/ኤድስ ያለበት ሰው የህክምና ክትትል በማድረግ መኖር ይችላል።

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

- ከመገናኛ ቴክኖሎጂ መረጃዎች የመንገድ ደኅንነትን በማየትና በመጠቀም የትራፊክ ደንቦችን በተገቢው መንገድ መግለጽ ይቻላል፡፡
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሕጻናት ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ በተመለከተ የበሽታው መተላለፊያ መንገዶችን በመለየት ተገቢ የጥንቃቄ መንገዶችን መከተል ያስፈልጋል፡፡
- ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሕጻናት ኀዘኔታና ፍቅር መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- የመንገድ ደኅንነትና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ተሻጋሪ ጉዳዮች ናቸው፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆነ" እዉነት" ትክክል ካልሆኑ " ሐሰት " በማለት መልሱ**

1. በተሽከርካሪ መንገድ ኳስ መጫወት ለአደጋ ያጋልጣል
2. የመንገድ ግራ አቅጣጫ ይዞ መጓዝ ከፊት ለፊት የሚመጣን መኪና ለማየት ይረዳናል።
3. የትራፊክ ምልክቶች ለእግረኞች አስፈላጊ አይደሉም።
4. ቀዩ የትራፊክ መብራት ቁም ማለት ነው።
5. አብሮ መመገብ ኤች አይ ቪ/ኤድስን አያስተላልፍም።

**ለ.ለሚከተሉት ጥያዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. የተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤ የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. በፍጥነት አለማሽከርከር

   ለ. ለእግረኛ ቅድሚያ መስጠት

   ሐ. ትራፊክ ደንቦችን አለማክበር

   መ. ሁሉም

2. በተሽከርካሪ የማይደርሰው የትኛው አደጋ ነው?

   ሀ. በውኃ መስጠም ለ. የንብረት መውደም

   ሐ. በፍጥነት መጓዝ መ. የቤተሰብ መበተን

3. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገድ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. አብሮ መብላት
ለ. አብሮ መጫወት
ሐ. የደም ንክኪ
መ. መጨባበጥ

4. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያ መንገድ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ከደም ንክኪ ራስን መጠበቅ

ለ. ምላጭና መርፌ በጋራ አለመጠቀም

ሐ. ከደም ንክኪ ራስን መጠበቅ

መ. ሁሉም

5. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥበላለባቸው ሕጻናት የምናሳየው ባህርይ ምንድን ነው?

ሀ. ፍቅር ለ. እንክብካቤ ሐ. ጎዘኔታ መ. ሁሉም

## ሐ.ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ

1. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያ መንገዶችን ዘርዝሩ፡፡
2. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሕፃናት ላይ የሚያደርሰው ተፅኖ ግለጹ፡፡

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



## ፍተሻ

ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለፅ የ "✓" ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ::

1. የመገናኛና ቴክኖሎጂ መረጃዎችን በማየትና በመጠቀም የትራፊክ ደንቦችን እገልጻለሁ:: ☐
2. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሕፃናት ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ እለያለሁ:: ☐
3. ኤች.አይ.ቪ.በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት ሀዘኔታና ፍቅር አሳያለሁ:: ☐

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource